# አማርኛ

# እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# ፬ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የተሰማማ


አስማምቶ አዘጋጆች፡-

ዳንኤል ኃይለ ኢየሱስ (MA)
ሕይወት ታምሩ (MA)
ሰለሞን ሰርካ (BA)

አርታኢ፡-

እንግዳወርቅ እንድርያስ

ሌያውት ዲዛይን፡-

ጌታሁን ታደሰ ኃይሉ



በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................V
ምዕራፍ አንድ ......................................................1
የአካባቢ ጥበቃ ......................................................1
ምዕራፍ ሁለት ......................................................14
የመንገድ ደህንነት ......................................................14
ምዕራፍ ሦስት ......................................................28
መረዳዳት ......................................................28
ምዕራፍ አራት ......................................................38
ሥርዓተ-ጾታ ......................................................38
ምዕራፍ አምስት ......................................................52
ጉብኝት ......................................................52
ምዕራፍ ስድስት ......................................................68
ስፖርት ......................................................68
ምዕራፍ ሰባት ......................................................84
ውሃ ......................................................84
ምዕራፍ ስምንት ......................................................98
መደራደር ......................................................98
ምዕራፍ ዘጠኝ ......................................................112
መገናኛ ብዙኃን ......................................................112
ምዕራፍ አስር ......................................................124
ንግድ ......................................................124
ዋቢ መጻሕፍት ......................................................139

# • መግቢያ

ውድ የተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ልጆቻችን የቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት በቤትዎ ውስጥ ልጅዎን ያግዙ፡፡

1. ለልጆችዎ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን. . .ይንገሯቸው /ያንብቡላቸው (እንዲያነቡ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩላቸው)፡፡
2. ለልጆችዎ የነገሯቸውን /ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ልጆችዎ መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
3. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው (ያስረዷቸው)፡፡
4. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
5. መምህራቸው በቤታቸው ተዘጋጅተው እንዲመጡ እና በተግባር እንዲያሳዩ የሚሰጣቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ለልጆችዎ በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎን ይወጡ፡፡

# ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ልጆቻችን የቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት በቤትዎ ውስጥ ልጅዎን ያግዙ፡፡

1. ለልጆችዎ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን. . .ይንገሯቸው /ያንብቡላቸው (እንዲያነቡ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩላቸው)፡፡
2. ለልጆችዎ የነገሯቸውን /ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ልጆችዎ መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
3. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው (ያስረዷቸው)፡፡
4. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
5. መምህራቸው በቤታቸው ተዘጋጅተው እንዲመጡ እና በተግባር እንዲያሳዩ የሚሰጣቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ለልጆችዎ በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎን ይወጡ፡፡

# ምዕራፍ 1

# የአካባቢ ጥበቃ

**የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የሚነበብላችሁን ምንባብ በማዳመጥ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበላችሁን ምንባብ በማንበብ ዋና ሃሳቡን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊና ፍካሬያዊ ፍቾ ትሰጣላችሁ፡፡
- አያያዥ ቃል በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ትጽፋላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

**አረንጓዴ ተክሎች**



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ከላይ የቀረበው የምንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ፎቶውን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?

ሐ. አረንጓዴ ተክሎች የምንላቸው ምን ዓይነት ተክሎች ናቸው?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. “አረንጓዴ ተክሎች በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ምንባብ ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. የአረንጓዴ ተክሎችን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡
2. አረንጓዴ ተክሎች ከሚባሉት ውስጥ አምስቱን ጥቀሱ፡፡
3. የአረንጓዴ ዕፀዋትና የሰዎች ትስስር በምንድነው?
4. ምንባቡ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድነው?
5. አረንጓዴ ተክሎችን ማጥፋት የሚያስከትለውን ጉዳት ዘርዝሩ?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሃሳቡ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሳችሁን በቃል ተናገሩ፡፡ በምክንያት አስደግፋችሁ ግለፁ፡፡

1. ወላጆቿ የቅድስትን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡
2. ቅድስት ገበያ ሄዳ የሚያስፈልጓትን ቁሳቁሶች ሁሉ ገዛች፡፡
3. እነቅድስት የሄዱበት ገበያ ገዥና ሻጩ ያለ ክርክር ይገበያዩበት ነበር፡፡
4. በላስቲክ የተወጠሩት ሸራዎች ውስጥ ሸቀጦች በብዛት ይታዩ ነበር፡፡
5. ቅድስት ገበያ ውስጥ ማስታወሻዋን ትፅፍ የነበረው በግሏ ማጥናት ስለፈለገች ነው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ:- ቃላት

ለ. “አረንጓዴ ተክሎች” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በ “ሀ” ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ”ለ” ስር ተመሳሳያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. የተሸፈነ | ሀ. ድርሻ |
| 2. አረንጓዴ | ለ. ለምለም |
| 3. እንዳይከሰት | ሐ. እንዳያጋጥም |
| 4. ተሳስረው | መ. ተያይዘው |
| 5. ሚና | ሠ. የተሞላ |

## መፃፍ

ሐ.የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፍራፍሬ | 3. አየር | 5.መኖር |
| 2. ደን | 4. ማገዝ | |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ቃላት

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በምሳሌው መሠረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሳሌ:- 1. ዛሬ ጠዋት ትኩስ ሻይ ጠጣሁ። የሚያቃጥል
2. የልጁ ጉልበት ገና ትኩስ ነው። አፍላ፣ ጠንካራ

1. ሉፓክ ዕቁብ ጣለ።

2. ሉፓክ በርሳውን ጣለ፡፡

3. ሉፓክ ራሱን ጣለ፡፡

4. በሁለቱ ጓደኛሞች ጠብ ምክንያት የክፍላችን ሰላም ደፈረሰ፡፡

5. ዝናቡ ከመጠን በላይ ስለዘነበ ወንዙ ደፈረሰ፡፡

ለ. በምሳሌው መሠረት ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊ (ቀጥተኛ) እና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

| ቃል | ቀጥተኛ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| ንብ | ማር የምትሠራ በራሪ ነፍሳት | ታታሪ |

| ቃል | ቀጥተኛ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| አንበሳ | | |
| ምላጭ | | |
| እባብ | | |
| ቆቅ | | |
| መሰላል | | |
| በግ | | |

# ክፍለ ትምህርት አራት

## 🎓 ሰዋስው

## አያያዞችን መለየት

አያያዥ ቃላት የምንላቸው ቃልን ከቃል ፣ ሐረግን ከሐረግ ፣ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር በማያያዝ አንድን ሐሳብ ከሌላ ሐሳብ

ጋር በማዋሀድ የሐሳብ ፍሰቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያገለግሉ ናቸው። አያያዥ ቃላት ከምንላቸው ውስጥም:- ስለዚህ፣ ነገር ግን፣ በመሆኑም፣ ይሁን እንጂ፣ የሆነው ሆኖ፣ ምክንያቱም፣ ስለሆነም፣ . . . ይገኙበታል።

ምሳሌ:- ሀ. ደቡብ ውስጥ ብዙ የሚጎበኙ ቦታዎች አሉ።

ለ. አይካ አንዱንም አልጎበኘም።

ደቡብ ውስጥ ብዙ የሚጎበኙ ቦታዎች አሉ፤ ይሁን እንጂ አይካ አንዱንም አልጎበኘም።

ሀ. ኡፋይሴ ዘወትር ታነባለች ።

ለ. ኡፋይሴ ጥሩ ውጤት አመጣች።

ኡፋይሴ ዘወትር ታነባለች፤ በመሆኑም ጥሩ ውጤት አምጥታለች።

ሀ. በምሳሌው መሠረት በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት በመለየት ጻፉ።

| ተ.ቁ | ዓረፍተ ነገር | አያያዥ |
|---|---|---|
| | ምሳሌ:- ነገ ወይም ከነገ ወዲያ አማርኛ ፈተና እንፈተናለን። | ወይም |
| 1 | እናቴ መጽሐፍ እና ቦርሳ ገዛችልኝ። | |
| 2 | ጎበዝ ነኝ ሆኖም በርትቼ አጠናለሁ። | |
| 3 | አያቴ ዛሬ ወይም ነገ ትመጣለች። | |
| 4 | ሰሚራ ብዙ ጊዜ ማጥናት እና መጫወት ትወዳለች። | |
| 5 | ብሩክ እና ጓደኞቹ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ። | |

ለ. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ጻፉ።

1. ነገር ግን 4. በመሆኑም

2. ስለዚህ
3. ምክንያቱም
5. ስለሆነም

ሐ. የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በመቀየር ፃፉ።

1. ሔኖክ ቁርሱን በላ።

ሔኖክ የተመገበው ምግብ አልተስማማውም።

2. ሽጊቱ ገበያ ሄደች።

ሽጊቱ ብርቱካን ገዛች።

3. የሒሳብ ትምህርት ይከብደኛል።

የሒሳብ ትምህርት ከማጥናት አልቆጠብም።

4. ሐያት ከክፍሏ አንደኛ ወጣች።

ሐያት ተሸላሚ ሆነች።

## ቃላት

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ።

1. ለምለም
2. መትከል
3. ጥቅም
4. መውሰድ
5. ሰጪ
6. ሙቀት

ሐ. ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- እና

ደንባሬ እና አመርጋ ጓደኞሞች ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ወይም | እስከ | እና |
| ስለዚህ | ነገር ግን | ግን |

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

### ሎረንሶ እና እኒቾ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከላይ የቀረበው የምንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ምስሉን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?

ሐ. የክፍላችሁን ንጽህና ለመጠበቅ ምን ታደርጋላችሁ?

መ. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ከሚገኙ ክበባት መካከል በየትኛው ክበብ ትሳተፋላችሁ?

ሎረንሶ እና እኒቾ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ሁለቱ ተማሪዎች ጓደኛሞች ሲሆኑ በትምህርት ቤታቸው ካሉት ክበቦች መካከል የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት ናቸው:: ሎረንሶ እና እኒቾ በዕቅዳቸው መሠረት በአካባቢ ጥበቃ ክበብ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመረዳዳት በዓመት ውስጥ ብዙ ተግባራትን አከናውነዋል::

የክፍል ጽዳትን መጠበቅና የትምህርት ቤቱን ግቢ ማስዋብ ከተግባራቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ከዚህም ባሻገር ከትምህርት ቤት ውጪም በተለያዩ የአካባቢ ጽዳቶች ላይ መሳተፍ የክበቡ ዓብይ ተግባር ነው::ሎረንሶ እና እኒቾ

በክበቡ ተግባራት ላይ በመሣተፍ የሥራ ድርሻቸውን ይወጣሉ:: እኒቾ በክበቡ ተጠሪነት፣ ሎረንሶ ደግሞ በክበቡ ፀሐፊነት ያገለግላሉ:: ሁለቱም የክበቡን አባላት የማስተባበር ልዩ ተሰጥኦ አላቸው:: ክበቡን የሚመሩና የሚያስተባብሩ መምህሮችም ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ዓመታዊ ዕቅዶችን ይነድፋሉ::
በዚህም መሠረት ዘወትር አርብ የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት የክፍል ፅዳት ተግባራትን የሚያከናውኑበት ቀን ነው:: እነ እኒቾ የእለቱን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በዕቅዳቸው መሠረት የመማሪያ ክፍላቸውን ለማፅዳት ተዘጋጁ:: በዚህ የፅዳት ቀን የክበቡ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በመረዳዳትና በመተሳሰብ በፅዳቱ ተግባር ላይ ይሳተፋሉ:: ይህ የሣምንቱ የክፍል የፅዳት ቀን ከሌሎቹ የፅዳት ቀናት ይለያል:: በሌሎቹ ቀናት ተማሪዎች በየተራ ክፍላቸውን በመጥረግና ቆሻሻዎችን በተዘጋጀላቸው ቦታ በመድፋት ያፀዳሉ::

ሀ. የእነ ሎረንሶ እና እኒቾ ክበብ ዓብይ ተግባር ምንድን ነው?

ለ. በመቀጠል ሎረንሶ እና እኒቾ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ምን የሚያከናውኑ ይመስላችኋል?

በዚህ የፅዳት ቀን ተማሪዎቹ ክፍሎቻቸውን መጥረግ ብቻ ሳይሆን የክፍሎችን ግድግዳዎች አጸዱ:: መስታወቶችን ወለወሉ:: ቆሻሻዎችንም በመሰብሰብ ከመምህሮቻቸው ጋር በመሆን በተገቢው መንገድ አስወገዱ:: በዚህ ዓይነት ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች መስታወቶች፣ ግድግዳዎችና ወለሎች በሚገባ ፀዱ:: ወንበሮችና ጠረጴዛዎችም በደንብ እየተደረደሩ ተወለወሉ:: በግድግዳዎችና በመስታወቶች ዙሪያ የነበ የሸረሪት ድርና አቧራ ተራገፈ::
ተማሪዎቹ በሠሯቸው ተግባራት በጣም ተደሰቱ:: ርስ በርስ በመረዳዳት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ተግባራትን በማከናወናቸው ለሌሎች ክበብ አባላት አርዓያነታቸውን አስመሰከሩ:: ከዚያም የሳምንቱ የትምህርት ቀን ማብቂያ በመሆኑ ሰኞ ለመገናኘት የስንብት ሰላምታ ተለዋውጠው ተለያዩ::

(በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር፤ በ2009 ዓ.ም፤ አጋዥ መጽሀፍ፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተስማምቶ የቀረበ::)

# ተግባር አንድ:- አንብቦ መረዳት

ሀ. "ሎረንሶ እና እኒቾ" በሚል ርዕስ በቀረበላችሁ ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ሎረንሶ እና እኒቾ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?
2. ሎረንሶ እና እኒቾ በትምህርት ቤታቸው የሚሳተፉበት ክበብ ምን ይባላል?
3. ተማሪዎቹ የሚያጸዷቸውን ስፍራዎች ዘርዝሩ?
4. ተማሪዎቹ በሌሎች ቀናት የክፍላቸውን ንጽህና እንዴት ይጠብቃሉ?
5. እናንተስ ከአሁን በኋላ በትምህርት ቤታችሁ እና በአካባቢያችሁ ምን ለማድረግ አሰባችኋል?

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ጽሕፈት

ለ. "ሎረንሶ እና እኒቾ" በሚል ርዕስ ከቀረበላችሁ ምንባብ ውስጥ ዋና መልዕክቱን በራሳችሁ አገላለጽ በአራት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

### ቃላት

ሐ. ባነበባችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ጻፉ።

| | |
|---|---|
| 1. አርዓያ | 5. ስፍራ |
| 2. መሰብሰብ | 6. ማብቂያ |
| 3. ማስዋብ | 7. ተለዋወጡ |
| 4. ዓቢይ | 8. በተገቢው |

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## ሰዋስው

## የዓረፍተ ነገር ምንነት

ዓረፍተ ነገር ማለት የተሟላ መልዕክት ማስተላለፍ የሚችል እና በስርዓት የተደረደሩ ቃላት ስብስብ ነው።

ምሳሌ፡-

ሀ. የአማርኛ ጽሁፎችን በሚገባ አነባለሁ። (ይህ ዓረፍተ ነገር ነው ምክንያቱም ቃላቱ በትክክለኛው ቅደም ተከተል ተደርድረዋል፤ ሙሉ ሃሳብም ተላልፏል።)

ለ. እህቴ ጽሁፍ። (ይህ ዓረፍተ ነገር አይደለም ምክንያቱም ሃሳቡ አልተሟላም።)

ሐ. የዚህ ክፍል ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው። (ይህ ዓረፍተ ነገር ነው ምክንያቱም ቃላቱ በትክክለኛው ቅደም ተከተል ተደርድረዋል፤ ሙሉ ሃሳብም ተላልፏል።)

ሀ. የሚከተሉት ጽሁፎች ዓረፍተ ነገር መሆናቸውን ወይንም ዓረፍተ ነገር አለመሆናቸውን በመለየት ጻፉ።

1. ርስ በርስ መረዳዳት የሚያኮራ ባህል ነው።
2. የአድዋ ድል በዓል 125ኛ ዓመት።
3. ባህላዊ ልብሶቻችን የማንነታችን መገለጫዎች ናቸው።
4. ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ።
5. በደቡብ ክልል ውስጥ በርካታ ብሔረሰቦች በአንድነት ይኖራሉ።
6. ግብር መገበር የዜግነት።

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## የዓረፍተ ነገር ምንነት

ዓረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚይዙት ግስ ብዛት አኳያ በሁለት ምድብ ይከፈላሉ ። እነሱም ነጠላ ዓረፍተነገር እና ዉስብስብ ዓረፍተነገር ናቸው።

### 1. ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡-

የሚባለው ዓረፍተ ነገሩ አንድ ግስ ብቻ በውስጡ የያዘ የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡- ሀ. ኮሮና ቫይረስ በአለም ላይ ተሰራጨ ።

ለ. ሃያት ወደ ትምህርት ቤት ሄደች ።

ሐ. ሜሮን መፅሐፍ ገዛች ።

### 2. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡-

የሚባለው ደግሞ በዓረፍተ ነገሩ ዉስጥ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ግሶችን የያዘ የዓረፍተነገር ዓይነት ነው ።

ምሳሌ፡-

ሀ. ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ተላላፊ በሽታ ስለሆነ መጠንቀቅ አለብን።

ለ. አመርጋ ኳስ መጫወት ቢችልም ብስክሌት ግን መንዳት አይችልም።

ሐ. ደራርቱ መጽሀፍ ገዝታ ለወንድሟ ሰጠችው።

ለ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ ዓረፍተ ነገር ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መሆናቸውን በመለየት ጻፉ።

1. ምግቡ ብዙ ዓይነት ስለሆነ ወዲያው ጠገብኩ።
2. ዘወትር አካባቢያችንን እናጸዳለን።

3. በርትታ ስለአጠናች ጥሩ ውጤት አስመዘገበች፡፡
4. ቁቱ እርሳሷን ሳትይዝ ትምህርት ቤት ሄዳለች፡፡
5. ላምቤቦ በጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡
6. ሀገሬን ከልቤ እወዳለሁ፡፡

ሐ. አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- እኔ እና ጓደኛዬ በጋራ እናጠናለን፡፡

መ.የሚከተሉትን መስተዋድዶች በክፍት ቦታው ላይ በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| እየ | ስለ | በ | ከ |

1. አይካ ብዙ ጊዜ_______ሚያነብ ጥሩ ውጤት አስመዘገበ፡፡
2. በጠዋት መነሳት______ፈለኩ እንቅልፍ ይጥለኛል፡፡
3. ዛሬ አባቴ_______መጣ መዝናኛ ቦታ ይወስደኛል፡
4. መንገዱ ስለማይመች_______መኪና አንሄድም፡፡

# የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬዊ ፍች ማለት ምን ማለት ነው?

   በምሳሌ አብራሩ?

2. አምስት መስተዋድዶችን ጻፉ::

3. - ስለዚህ
   - ቢሆንም
   - ነገር ግን

   በሚሉት አያያዥ ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ::

4. - ማገዝ
   - ልምላሜ
   - መጠን
   - ዕቅድ

ለሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ስጡ::

5. - ማስዋብ
   - መጉዳት
   - ማብቂያ

ለሚሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ::

6. - ቋንጣ
   - ዱባ

ለሚሉት ቃለት ቀጥተኛ እና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ::

7. ነጠላ እና ውስብስብ ዓፍተ ነገሮችን ጻፉ::

# ምዕራፍ 2

# የመንገድ ደህንነት

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- መንገድ ላይ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን ትናገራላችሁ።
- የትራፊክ አደጋ የሚደርስበትን መንገድ ታብራራላችሁ።
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ ።
- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

### "የመንገድ ላይ ጥንቃቄ"





## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ከላይ የቀረበው ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ፎቶዎቹን በማየት የተረዳችሁትን ግለጹ?

ሐ. የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ስለመንገድ አጠቃቀም የምታውቁትን ግለጹ?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. “የመንገድ ላይ ጥንቃቄ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. የአስፓልት መንገድ ስንሻገር ማቋረጥ ያለብን በምን ዓይነት ቦታ ላይ ነው?
2. አረንጓዴ መብራት ሲበራ ተራው የማን ነው?
3. ቀይ መብራት ሲበራ ተራው የማን ነው?
4. በመንገድ ላይ ስንጓዝ የትኛውን አቅጣጫ መከተል አለብን? ለምን?

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

1. መንገድ ስናቋርጥ ግራና ቀኝ መመልከት አግባብ አይደለም።
2. አሽከርካሪዎች ሁልጊዜ ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
3. መንገድ ስንጓዝ ለእግረኞች ብቻ ተብሎ በተዘጋጀ መንገድ መሄድ ተገቢ ነው።
4. ሾፌሮች በፍጥነትና ጠጥተው ቢያሽከረክሩ ምንም አይነት ጉዳት አይደርስባቸውም።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. “የመንገድ ላይ ጥንቃቄ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. አግረኞች | 3. መጠቀም | 5. ጥንቃቄ |
| 2. አያሌ | 4. ማቋረጥ | 6. በትኩረት |

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ይገባል፡፡
2. የመኪና መንገድ ለማቋረጥ የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች አሉ፡፡
3. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡
4. እግረኞች ለእግረኛ ተብሎ የተዘጋጀ መንገድ መጠቀም አለባቸው፡፡
5. የመንገዱን ግራና ቀኝ መቃኘት አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

1. በመንገድ ላይ ስንሄድ መሮጥ የለብንም፡፡
2. በአከባቢያችን በርካታ ተሽከርካሪዎች አሉ፡፡
3. በሳምንት አንድ ቀን ሽርሽር እሄዳለሁ፡፡
4. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡
5. የመንገድ ላይ አደጋዎች አሳሳቢ ሆነዋል፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ጽሕፈት

ሀ. "የመንገድ ላይ ጥንቃቄ" በሚል ርዕስ ካዳመጣቻሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሐሳብ በአራት ዓረፍተ ነገር ጻፉ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ለ. ለሚከተሉት ዝርዝር ሐሳቦች በምሳሌው መሠረት መልስ መሆን የሚችሉ ቃላትን ለመመስረት በተሰጠው የአቅጣጫ መጠቆሚያ መሠረት አንዳአንድ ፊደላትን ወደ ጎን እና ወደታች በመልስ መስጫ ሳጥኑ ውስጥ ጻፉ።


### ወደ ጎን

| ቁጥር | መግለጫ |
|---|---|
| 1 | ለአገር እና ለወገን መልካም ተግባርን ያከናወነ ሰው፤ |
| 3 | አበባ የምትቀስም እና በታታሪነት የምትጠቀስ ነፍሳት፤ |
| 4 | ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ የአገራችን ጥንታዊ ሃውልት፤ |
| 7 | ከመሬት ውስጥ የሚገኝ የዕፀዋት ክፍል፤ |
| 8 | ንጽህናን ለመጠበቂያነት የሚያገለግል አረፋ ያለው ጠጣር ቁስ፤ |
| 9 | በምንተኛበት ጊዜ ለጭንቅላት መደገፊያነት የሚያገለግል፤ |

## ወደ ታች

| ቁጥር | መግለጫ |
|---|---|
| 2 | ግንብ የመገንባት ሙያ ያለው ሰው፤ |
| 4 | የእናት ወይም የአባት እህት ፤ |
| 5 | ባለስድስት አውታር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ፤ |
| 6 | በአንድ በኩል የተቦረቦረና የተለያዩ ነገሮች ተጨምረውበት የሚወቀጥበት የቤት ዕቃ፤ |
| 10 | በሁለቱም እግሮቻችን በማስገባት እግሮቻችንን በሙሉ የሚሸፍን የልብስ ዓይነት፤ |

## የመልስ መስጫ ሳጥን



# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

## የሾፌሩ ታሪክ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. አሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው ለማን ነው? ለምን?

ለ. የትራፊክ አደጋ በምን ምክንያት የሚደርስ ይመስላችኋል?

የ38ዓመት ጎልማሳ ነኝ። ድፍን አስር አመታትን በታክሲ ሾፌርነት አገልግያለሁ።ተወልጄ ያደኩት በዲላ ከተማ ነው። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በዚሁ በዲላ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተምሬአለሁ። በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ባልባልም ከሠነፎች ተርታ የምመደብ አልነበርኩም። ለቤተሰቦቼ ብቸኛ ልጃቸው ነኝ።የቤተሰቦቼ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ስለነበር ኑሯችንን ለማሻሻል በማሰብ መንጃ ፈቃድ አውጥቼ በታክሲ ሾፌርነት እየሠራሁ የራሴንና የቤተሰቤን ገቢ መደጎም ጀመርኩ። ሥራዬ የታክሲ ሾፌር በመሆኑ በየቀኑ ከበርካታ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ እድል

ፈጠረልኝ፡፡ ጊዜየን ባግባቡ ስለምጠቀም ጥሩ ገቢ ማግኘት ቻልኩ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን የተለያዩ ሱሶችን መላመድ ጀመርኩ፡፡ ጫት መቃምን እና አልኮል መጠጣትን ቋሚ ሥራዬ በማድረግ ወደ ቤት በጊዜ መግባትን አቆምኩ፡፡ አንድ ቀን ግን እንደተለመደው ከሥራ መልስ ወደ መጠጥ ቤት ስገባ የልጅነት የትምህርት ቤት ጓደኛዬን ሲጠጣ አገኘሁት፡፡ ከጓደኛዬ ጋር የተገናኘሁት ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለሆነ ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥንና አብረን መጠጣት ጀመርን፡፡ እየጠጣን ካመሸን በኋላ ጓደኛዬን ቤቱ ለማድረስ ታክሲዬን አስነስቼ ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት እየነዳሁ ጉዞአችንን ቀጠልን፡፡ አንዳንዴም እየሳቅንና ሙዚቃ እያዳመጥን ስንሄድ በድንገት ከቆመ ገልባጭ መኪና ጋር ተላተምን፡፡

1. ከዚህ በኋላ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?
2. ጠጥቶ መንዳት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ለምን?

ከወር በኋላ ራሴን በወላይታ ክርስቲያን ሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ አገኘሁት፡፡ እንደ ነቃሁ የጓደኛዬ ሕይወት ላይመለስ እስከ ወዲያኛው ማሸለቡን ነገሩኝ፡፡ እኔም የቀኝ የሰውነት ክፍሌን ማንቀሳቀስ አቅቶኝ የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ቀረሁ፡፡
ጠጥቼ በማሽከርከሬ እና የትራፊክ ሕጎችን ባለማክበሬ ለወላጆቼ ተጨማሪ ሸክም ሆንኩ፡፡ በየቀኑ እንደ እኔ የትራፊክ ደንብን ባለማክበርና ጠጥቶ በማሽከርከር የሚጠፋውን የሰው ሕይወት፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ሳስብ ከፍተኛ ጥፋተኝነት ይሰማኛል፡፡ አሽከርካሪዎችም ጉዳት ከመድረሱ በፊት ጥንቃቄ እንድታደርጉ፣ ከእኔ ተማሩ! እላለሁ፡፡

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. “የሾፌሩ ታሪክ” በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ባለታሪኩ ስንት ዓመቱ ነው?
2. ባለታሪኩ የምን ሾፌር ነበር?

3. አደጋው በደረሰበት ወቅት የሾፌሩ ጓደኛ የተቀመጠው በየት አቅጣጫ ነበር? ለምን?
4. የባለታሪኩ የኑሮ ደረጃ በምን ዓይነት ሁኔታ ቀጠለ?
5. በምንባቡ መሠረት ሾፌሩ የመኪና አደጋ የደረሰበት ለምን ይመስላችኋል?

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ቃላት

ሀ. በምንባቡ መሠረት በ" ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መደኅም | ሀ. ሳይታሰብ |
| 2. በርካታ | ለ. መርዳት |
| 3. በድንገት | ሐ ረድፍ (ምድብ) |
| 4. ተላተምን | መ. ብዙ |
| 5. ተርታ | ሠ. ተጋጩን |

ለ. ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. አሳዛኝ | 3. ዝቅተኛ | 5. መጥፎ |
| 2. መቀነስ | 4. ኀበዝ | 6. ገቢ |

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## መናገር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የመወያያ ርዕስ መሠረት በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ የውይይታችሁን ሐሳብ አካፍሉ፡፡

# ንባብ

## አቀላጥፎ ማንበብ

### አንበሳ

አንበሳ በድመት ዘር ውስጥ ካሉት እንስሳት ግርማ ሞገስ ያለው፣ ኃይለኛና አስፈሪ ከሩቅ ሲመለከቱት ደስ የሚል አውሬ ነው፡፡ ቁመቱ እስከ አንድ ሜትር፣ ርዝመቱ (ጅራቱን ሳይጨምር) ሁለት ሜትር ይደርሳል፤ ክብደቱ እስከ 236 ኪሎ ግራም ይመዝናል፡፡ ሆዱ ላይ ትንሽ ነጣ ከማለቱ በቀር ጸጉሩ ወርቃማ ቢጫ ነው፡፡ ሲያረጅ ጎፈሩ ይጠቁራል፡፡ ጅራቱ ረጅም፣ ጭራው አጭርና ጥቁር ነው፡፡ ሴቷ አንበሳ ከወንዱ አነስ ብላ ዘለግ ያለች ነች፤ ጎፈር የላትም፡፡ የአንበሳ የእርግዝና ወቅት አራት ወር ሲሆን በአንድ ጊዜ ከ2 እስከ 4 ደቦሎችን ትወልዳለች፡፡ አንበሳ እስከ 25 ዓመት እድሜ ይኖራል፡፡

(ለማ ጉያ፣1995፣ ያላስተማሪ የሥዕል ትምህርት መማሪያ፣ ገጽ 84፤
ለንባብ ትምህር እንዲያመች ተደርጎ የቀረበ)

ለ. ከላይ ካነበባችሁት ምንባብ ውስጥ የተረዳችሁትን መልእክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሰባት


## ቃላት

ሀ. በየሳጥኑ ዙሪያ ላሉት ቃላት ተመሳሳይ የሚሆነውን ቃል ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ ሳጥኑን አሟሉ፡፡


## የተሰጡ አማራጭ ቃላት

ማጽዳት ረጅም ደግነት ማሰብ


1.





2.




3.




4.



# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ሰዋስው

### ሀ. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመግባት ሐሳቦችን ሊያሟሉ የሚችሉ ቃላትን ምረጡ፡፡

1. ሴቶችም ____________ወንዶች እኩል የሆነ መብት አላቸው፡፡

   ሀ. ቢሆኑም ለ ነገርግን ሐ ሆኑ መ. ስለዚህ

2. ህንፃው ተሰርቶ ከተጠናቀቀ ቆይቷል፤__________እስከ አሁን አገልግሎት መስጠት አልጀመረም፡፡

   ሀ. ነገርግን ለ. ወይም ሐ. ስለዚህ መ. ሆኖም

3. አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጌአለሁ_____ፈተናውን በድል አጠናቅቃለሁ፡፡

   ሀ. ነገርግን ለ. ስለዚህ ሐ. ሆኑ መ. ወይም

4. በሚቀጥለው ሳምንት __________ጂንካ መሄዴ አይቀርም፡፡

   ሀ. ሲሆንም ለ. ወይም ሐ ደግሞ መ. ወደ

5. ጀማል የእግር ኳስ ተጫዋች ሲሆን ፋጡማ__________ሯጭ ናት፡፡

   ሀ. ደግሞ ለ. ስለዚህ ሐ. ወይም መ. ነገርግን

### ለ. የሚከተሉትን ቃላት በባዶ ቦታዎች ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹን አሟሉ፡

ጨዋታዎች ማስተማር ማታ መንገዶች
መማር እንዳይሰደዱ አጠገብ ክብር

1. ዘወትር______________ትምህርቴን አጠናለሁ፡፡
2. ትምህርታችንን በትጋት______________አለብን፡፡
3. ልጆች የሚጫወቷቸው በርካታ_________________አሉ፡፡
4. የዱር እንስሳት _____አካባቢያችንን መንከባከብ አለብን፡፡
5. የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ____________በማወቅ ጥንቃቄ እናድርግ፡፡

6. የምናውቀውን ለማያወቁት _______________ እንችላለን፡፡
7. ለወላጆቻችን ተገቢውን ______________ መስጠት አለብን፡፡

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ጽሕፈት

ሀ. ከሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ብቻ በመለየት ጻፉ፡፡

አርባ ምንጭ በደቡብ ከሚገኙ ከተሞች አንዷዋ ናት፡፡ በከተማዋ ስለመንገድ ደህንነት በተመለከተ በተለያየ መንገድ ትምህርት ይሰጣል፤ ይሁን እንጂ በርካታ የትራፊክ አደጋዎች ያጋጥማሉ፡፡ ለትራፊክ አደጋ እንደ መንስኤ ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የመንገድ ህጎችን አለማወቅ ነው፡፡ አሽከርካሪዎችና እግረኞች በሙሉ የመንገድ አጠቃቀም ህጎችን ማወቅ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለመፍጠር ባለድርሻ አካላት ሁሉን አቀፍ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፤ ቢሆንም ህብረተሰቡ የግንዛቤ ለውጥ አላመጣም፡፡

ለ. በምሳሌው መሠረት የተዘበራረቁትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስተካከል የተሟላ ሐሳብ የሚያስተላልፍ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡-

ንጽህና / የክፍላችን / እንጠብቃለን / እኛ

- እኛ የክፍላችንን ንጽህና እንጠብቃለን፡፡

1. እኔ / ነኝ / ክፍል / ተማሪ / የአራተኛ
2. ባህላችንን / የማክበር / እንግዳ / ልናዳብር / ይገባል
3. ጳጉሜ / ነው / የአመቱ / ወር / የመጨረሻ
4. ምቹ / መንገዱ / አይደለም / ለመኪና
5. ረጅሙ / በአለማችን / ወንዝ / ነው / አባይ

ሐ. በምሳሌው መሠረት የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም በእያንዳንዳቸው ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

እና ነገርግን ስለዚህ ብሆንም

# የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች ስጡ

   ሀ.ሀሴት ሐ. ልጅ እግር

   ለ.ቀጠፈ መ. ሀሩር

2. መስተዋድዶችን በመጠቀም አምስት ዓፍተ ነገሮችን መስርቱ።
3. አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።
4. የንባብ ችሎታችሁን ለማዳበር መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት የቀረበላችሁን ምንባብ ተለማመዱ፤ ለክፍል ጓደኞቻችሁም ተራ በተራ አንብቡ።

   ሀ. ዜይነባ ዘወትር ታጠናለች፤ በመሆኑም ጥሩ ውጤት ታስመዘግባለች።

   ለ. ከነገወዲያ የሩጫ ውድድር አለብኝ፤ ስለዚህ የስፖርት ትጥቄን ማጠብ አለብኝ።

# ማርስ

ከፕላኔቶች መሀል ከፀሀይ ርቃ የምትገኘው ማርስ ናት። የጥንት ሮማዊያን ማርስ ብለው የሰየሟት በጦር አምላካቸው ስም ነው። ማርስ ከመሬት ጋር ብትመሳሰልም ልዩነቶች ግን አላት። ለምሳሌ ማርስ ከመሬት ታንሳለች። መሬትን አንድ አስረኛ ነው የምታክለው። ማርስ ቀላ ያለች ስተሆን፣ዋልታወቿ ነጣ ያሉ ናቸው።

ማርስ ላይ ሸለቆዎች፣ ሜዳዎችና ተራራማ ቦታዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ማርስ ወገብ አካባቢ ትልቅ ሸለቆ ይገኛል። የዚህ ሸለቆ ርዝማኔ 5 ሺህ ኪሎ ሜትር ሲሆን፣ የጎን ስፋቱ 100 ኪሎ ሜትር ነው። ጥልቀቱም 10 ኪሎ ሜትር ይሆናል። የማርስ ትልቁ ተራራ ኦሊምፐስ በመባል ይታወቃል። ከፍታውም 25 ኪሎ ሜትር ይሆናል። በመሬት ላይ የሚገኘው ትልቁ ተራራ ኤቨረስት በመባል ይታወቃል። በማርስ ገጽታ ሌላም የሚታይ ነገር አለ። እሱም የወንዝ መውረጃ የመሰለ ጉድጓድ ነው። ይህ የወንዝ መውረጃ ጎደጓዳማ

ስፍራም “በአንድ ወቅት ማርስ ላይ ውሀ እነደነበር ያስረዳል፡፡” በማለት የስነፈለክ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡

ማርስ አካባቢ አየር አላት፡፡ ከባቢ አየሩዋም እነደ ቬነስ ከባቢ አየር ጥቅጥቅ ያለ ሳይሆን በጣም ስስ ነው፡፡ የተሰራውም በአብዛኛው ካርቦንዳይኦክሳይድ ከተባለው ጋዝ ነው፡፡ጥቂት ይሁኑ እንጅ ናይትሮጂን ፣ኦክስጅን እና ውሀ ይገኙበታል፡፡ በይዘትም ከመቶ 95 እጅ ካርቦንዳይኦክሳይድ ነው፡፡ የሚዘዋወር ጥቂት ደመናም አለ፡፡ ሆኖም ይህ ደመና ዝናብ የማዝነብ አቅም ያለው አይደለም፡፡በዚህም ምክንያት በማርስ ላይ ዝናብ አይዘንብም፡፡ሆኖም ብዙውን ጊዜ የማርስን ሽለቆዎች በጭጋግ ተሸፍነው ነው የምናያቸው፡፡

ማርስ ከሌሎች ቅርብ ፕላኔቶች ይበልጥ ከፀሐይ፣ ከሜርኩሪ፣ከቬነስና ከመሬት የበለጠ ትቀዘቅዛለች፡፡የማርስ ሙቀት ቀን ከ00c ጥቂት ከፍ ሲል፣ በምሽት ወቅት ከዜሮ በታች 200c ይወርዳል፡፡ይህም ቅዝቃዜ መሬት ላይ በብዙ ቦታዎች የሚታይ አይደለም፡፡

ማርስ ሁለት ትናንሽ ጭፍራዎች አሉዋት፡፡እነርሱም ፎቦስና ዴይሞስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

(ምንጪ፡- እሸቱ አሰፋ፣2000፣ፕላኔቶችና ሌሎች የሰማይት አካለት፣ገጽ 51- 54)

5. “ማርስ” በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የተረዳችሁትን መልዕክት በአራት ዓረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

# ምዕራፍ 3

# መረዳዳት

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ የምንባቡን መልዕክት ትናገራላችሁ፡፡
- ከቃላት ውስጥ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን ታወጣላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን ነጥላችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ከተሰጣችሁ ጽሑፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

### እህትማማቾቹ



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ከላይ የቀረበው ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ምሥሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለጹ?

ሐ. መረዳዳት ከየት ይጀምራል?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. "እህትማማቾቹ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. ጀሚላ ሎሚን የምትበልጣት በስንት ዓመት ነው?
2. ጀሚላ ሎሚን "አንቺ እኮ እስትንፋሴ ነሽ።" ስትል ምን ለማለት ፈልጋ ነው?
3. ሎሚ ወደበሩ የሮጠችው ለምንድን ነው?
4. እናንተ በቤት ውስጥ በእቅማችሁ ምን ምን ሥራዎችን ትሠራላችሁ

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. "እህትማማቾቹ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | " ለ " |
|---|---|
| 1. መብለጥ | ሀ. ልዩነት |
| 2. አንድነት | ለ. ቆሸሾ |
| 3. ፍቅር | ሐ. መዘንጋት |
| 4. ጸድቶ | መ. ማነስ |
| 5. ማስተዋል | ሠ. ጥላቻ |

ለ. "እህትማማቾቹ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳያቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

ቤቱን በተቻለኝ አቅም በዚህ መልኩ <u>አዘጋጀሁት</u>፡፡ አስተካከልኩት

1. ሎሚ ቤቱን <u>ወልውላ</u> ሶፋውን እና ጠረጴዛዎችን አስተካከለቻቸው፡፡
2. ወዲያውኑ የግቢያቸውን በር ለመክፈት ወደበሩ <u>ተፈተለከች</u>፡፡
3. ጀሚላ በታናሽ እህቷ <u>በመገረም</u> "አንቺ እኮ እስትንፋሴ ነሽ" አለቻት፡፡
4. ጀሚላ የራሷን የቤት ሥራ <u>ከጨረሰች</u> በኋላ ሎሚን ታስጠናታለች፡፡
5. ቤቱን ለማስተካከል <u>እየተቻኮለች</u> ወደ ሳሎን ገባች፡፡

ሐ. በምሳሌው መሠረት ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፤ በመቀጠልም በሰጣችሁት ፍች ዓረፍተነገር መስርቱ፡

ምሳሌ፡- ሃሴት = ተመሳሳይ ፍች፡- ደስታ
ተቃራኒ ፍች፡- ሐዘን

ሀ. ሁሌም በቤታችን ትልቅ ደስታ አለ፡፡

ለ. በባህላችን ሐዘን ሲያጋጥም ነጠላ ተዘቅዝቆ ይለበሳል፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ትልቅ | 3. ቆሸሸ |
| 2. አጭር | 4. ፈጣን |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ንባብ

## የመረዳዳት ጥግ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የመረዳዳት ጥግ የሚለው የንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ከላይ የምትመለከቱት ፎቶግራፍ የማን ነው?

ሐ. መረዳዳት ማለት ምን ማለት ነው?

ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በቀድሞው ሸዋ ክፍለ ሃገር በሰላሌ አውራጃ ልዩ ስሙ ሸበል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተወለዱ፡፡ ወይዘሮ አበበች የአብራካቸው ክፋይ የሆነ አንድም ልጅ የላቸውም፡፡ ወይዘሮ አበበች አጠር ያሉ የቀይ ዳማ ሲሆኑ ደግነት፣ መንፈሳዊነት፣ ሩህሩህነትና አዛኝነት ከፊታቸው ላይ ይነበባል፡፡ በተለይ ትህትናቸው ከልብ ነው፡፡ የወይዘሮ አበበችን የሕይወት አቅጣጫ የለወጠው የወሎ ጉዟቸው ነበር፡፡ መስከረም 14 ቀን 1972 ዓ.ም ግሸን ማርያምን ሊያነግሱ ወደ ወሎ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደ ግሸን የተጓዙት ወይዘሮ አበበች ወሎ ተከስቶ በነበረው ድርቅ ምክንያት ባዩትና ባስተዋሉት ነገር መንፈሳቸው ተነክቶ የሙት እናቷን ጡት እየጠባች ያገኟትን ህፃን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

ሀ. ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና የት ተወለዱ?

ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

ከዚህ በኋላ ከትዳራቸውና ከዘመዶቻቸው ይልቅ ዘመድ አልባና ምንም ደጋፊ የሌላቸውን ልጆች መረጡ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ 21 ህፃናትን ይዘው መኖር ሲጀምሩ፣ የ21 ህፃናትን ጉሮሮ ለመድፈን፣ አልባሳትን ለማሟላት በመጀመሪያ የነበሯቸውን ልዩ ልዩ ወርቅ አና ጌጣጌጦች ሸጡ፡፡ በገንዘቡ እህል ሸምተው እንጀራና ዳቦ እየጋገሩ፣ ቆሎ እየቆሉ መሸጡን ተያያዙት፡፡ በሚገኘው ትርፍም ልጆቻቸውን መመገብና ማልበስ ቻሉ፡፡ በጥቂት ህፃናት የተጀመረው ሰብዓዊ ተግባር በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ አድጎ በብዙ ማህበረሰባዊ እድገትና ልማት ውስጥ ተስፋፍቶ ማህበረሰቡን ለለውጥና ለእድገት በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የድርጅቱ መጠሪያ በአሁኑ ጊዜ አበበች ጎበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር በመባል ይታወቃል፡፡ ወይዘሮ አበበች ጎበና ለሃገርና ለወገን ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ የጅማ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል፡፡ ድርጅታቸው ለሰብዓው ድጋፍና እንክብካቤ ላደረገው አስተዋጽኦ በየጊዜው ከተለያዩ አለማቀፍና አገር አቀፍ ድርጅቶች በርካታ ዋንጫዎችንና የምስክር ወረቀቶችን አግኝቷል፡፡ ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና በ85 ዓመታቸው ሰኔ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ቀን ድረስ ድርጅቱን በዋና ሥራ አስኪያጅነት ሲመሩ ነበር፡፡

ምንጭ፡- ሺበሺ ለማ (2007ዓ.ም)፣ አርዓያዎቹ ለክፍል ደረጃው እንዲያመች ተደርጎ የቀረበ

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. "የመረዳዳት ጥግ " በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. አበበች ጎበና የት አካባቢ ተወለዱ?
2. ከትዳራቸውና ከዘመዶቻቸው ይልቅ ምንም ደጋፊ የሌላቸውን ልጆች ለምን መረጡ?
3. ለአገርና ለወገን ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ ምን አገኙ?

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ፡፡

1. የወይዘሮ አበበችን የሕይወት አቅጣጫ የቀየረው ምን ነበር?
   ሀ. የቤተሰባቸው ፍቅር ሐ. የዘመዶቻቸው ግፊት
   ለ. የወሎ ጉዟቸው መ. ልጅ ስለሌላቸው
2. ከሚከተሉት መካከል የአበበች ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ደግነት ሐ. ጨካኝነት
   ለ. ሩህሩህነት መ. አዛኝነት
3. ወይዘሮ አበበች የህፃናትን ምግብና አልባሳት ለማሟላት ምን ያደርጉ ነበር?
   ሀ. የወርቅ ጌጣጌጣቸውን ሸጠዋል፡፡
   ለ. ቆሎ እየቆሉ ይሸጡ ነበር፡፡
   ሐ. ዳቦ እየጋገሩ ይሸጡ ነበር፡፡
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው፡፡
4. የወይዘሮ አበበች ድርጅት መጠሪያው ምን የሚል ነው?
   ሀ. አበበች ጎበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር
   ለ. የአበበች ጎበና በጎ አድራጎት ማህበር
   ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅት
   መ. አበበች ጎበና የሃብታሞች ድርጅት
5. ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለወይዘሮ አበበች ጎበና የከብር ዶክትሬት ዲግሪ የሰጣቸው በምን ምክንያት ነው?
   ሀ. ዩኒቨርሲቲውን በሥራ ስለሚደግፉት
   ለ. ለአገርና ለወገን ባበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ
   ሐ. ዩኒቨርሲቲውን በገንዘብ ስለሚደግፉት
   መ. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ገብተው ስላስተማሩ

# ክፍለ ትምህርት አራት

# አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት "የመረዳዳት ጥግ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተራ በተራ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ።

## ቃላት

ሀ. በምንባቡ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አቅጣጫ | ሀ. ገዝተው |
| 2. ሸምተው | ለ. ጊዜ |
| 3. ወቅት | ሐ. የቀየረው |
| 4. የላቀ | መ. መስመር |
| 5. የለወጠው | ሠ. ከፍ ያለ |

## ክፍለ ትምህርት አምስት

## ጽሕፈት

ሀ. "የመረዳዳት ጥግ" ከሚለው ምንባብ ውስጥ ያገኛችሁትን ሐሳብ በአራት ዓፍተነገሮች ጻፉ።

ለ. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኘው የበጎ አድራጎት ክበብ የሚያከናውነውን ተግባር በተመለከተ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

# ሰዋስው

## ቅጥያዎች

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመነሻ ቅጥያዎች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- እንደመጣ እንደ-

1. ስለተከለ
2. አስቀረ
3. እየፈጠረ
4. በፍጥነት
5. ሲሄድ
6. ከሰጠ
7. እንደፅጽዋት
8. ስለቤተሰብ
9. ቢቀር
10. አስመለሰ

ለ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመድረሻ ቅጥያዎች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ልጁ = -ኡ

1. ተማሪዎች
2. ልብስህ
3. በሬዎች
4. መምህሮች
5. መጽሀፌ
6. ክፍላችን
7. ድመቶች
8. እርሳስሽ
9. ቤቱ
10. ሥራችሁ

ሐ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በምሳሌው መሠረት በመነጣጠል ጻፉ።

| | ባለቅጥያ ቃላት | የመነሻ ቅጥያ | ዋና ቃል | የመድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለልብሶች | ስለ- | ልብስ | -ኦች |
| 2 | ከተወች | | | |
| 3 | በደብተሩ | | | |
| 4 | የአገራችን | | | |
| 5 | እንደሰጠን | | | |
| 6 | አልመሰለም | | | |

መ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡
፡

ምሳሌ:- የባህላችን

- ምግባችን የባህላችን መገለጫ ነው።

ሠ. በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለዩ፤ በመቀጠልም የለያችኋቸውን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ደጊቱ በትምህርቷ ጥሩ ውጤት ታስመዘግባለች። ምክንያቱም ከመምህሮቿ የሚሰጣትን ገለጻ በሚገባ ትከታተላለች። የክፍል እና የቤት ሥራዋን በመሥራት ታጠናለች። በባህሪዋም የተመሰከረላት ጨዋ ተማሪ ናት። ስለሆነም በሰዎች ዘንድ የተወደደች ናት። መምህሮቿ "ጥሩ ስነ-ምግባር ያስከብራል፤ ነገር ግን የባህሪ ችግር ያለበት ተማሪ በሰዎች ዘንድ አይወደድም።" የሚሏትን ምክር ለጓደኞቿ ትነግራቸዋለች።ስለዚህ ሁላችንም በስነ-ምግባር መታነፅ አለብን።

## የምዕራፍ ሦስት የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች ስጡ:: በመቀጠልም በፍቻቸው ነጠላ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ::

   ሀ. ሰበሰበ ለ. ራቀ ሐ. ፍቅር

2. ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የመነሻ ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?
4. የመድረሻ ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?
5. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመነጣጠል ጻፉ::

| | ባለቅጥያ ቃላት | የመነሻ ቅጥያ | ዋና ቃል | የመድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለህዝባችን | | | |
| 2 | እንደችሎታሽ | | | |
| 3 | በመጽሀፉ | | | |
| 4 | ከቀረሽ | | | |

6. አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ
7. በቤታችሁ ውስጥ ቤተሰቦቻችሁን በሥራ በማገዝ ያከናወናችኋቸውን ተግባራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::

# ምዕራፍ 4

# ሥርዓተ-ጾታ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች


ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ርዕሱን በመመልከትና በማዳመጥ ሃሳባችሁን ታካፍላላችሁ።
- ካነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ ዝርዝር መረጃውን ትጽፋላችሁ።
- ስለአንቀጽ ምንነት ታብራራላችሁ።
- የውሰት ቃላትን ጥቅም ትዘረዝራላችሁ።
- የግስንና የስምን ምንነት ትገነዘባላችሁ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

#### የሥራ ክፍፍል



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የሥራ ክፍፍል ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ሥዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለጹ?

ሐ. በቤታችሁ በአብዛኛው የቤት ውስጥ ሥራ የሚሰራው ማን ነው?ለምን?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. "የሥራ ክፍፍል" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የእህትዬዋ የትምህርት ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣው ለምንድን ነው?
2. እህትዬዋ በክበቡ ስለምትሳተፍ በርካታ ቁምነገሮችን ተምራለች ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. እህትዬዋ የተቆጨችው በምን ምክንያት ነው?
4. አባትየው የሥራ ክፍፍልን በተመለከተ ምን ዓይነት አመለካከት ያላቸው ይመስላችኋል?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. "የሥራ ክፍፍል" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | " ለ " |
|---|---|
| 1. አካባቢ | ሀ. ማወቅ |
| 2. መማር | ለ. መጸጸት |
| 3. ተረዷት | ሐ. አመለካከት |
| 4. መቆጨት | መ. ሠፈር |
| 5. አስተሳሰብ | ሠ. መተባበር |
| | ረ. ተገነዘቧት |

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. የበለጠ | 3. ለቀቀ | 5. በቡድን |
| 2. በቅርብ | 4. ርህራሔ | |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ጽሕፈት

ሀ. ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. መቀነስ | 3. አባላት | 5. ጫና |
| 2. ክበብ | 4. ሥራ | |

ለ. በቤታችሁ በጾታ እኩልነት ላይ የተመሰረተ የሥራ ክፍፍልን የሚያሳይ ጽሑፍ በአራት ዓረፍተ ነገር በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ቃላት


ሀ. አማርኛ ቋንቋ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ቋንቋዎች በመዋስ እየተጠቀመባቸው ያሉ ቃላትን ከመጻሕፍት እና ሰዎችን በመጠየቅ ከሰበሰባችሁ በኋላ ማስታወሻ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

ለ. በየሳጥኑ መሃል ላሉ ቃላት ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተመሳሳይ የሚሆኑትን አራት ቃላት በመምረጥ በእያንዳንዱ ሳጥን ዙሪያ አሟሉ፡፡


**የተሰጡ አማራጭ ተመሳሳይ ቃላት**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፌሽታ | መድከም | ከመረ | በተነ | ፈጸመ |
| አስተላለፈ | ቆለለ | መኳተን | ፈንጠዝያ | አዳረሰ |
| አከናወነ | አጠራቀመ | አስፋፋ | ሀሴት | መልፋት |
| አጠናቀቀ | ፍስሃ | አከማቸ | መትጋት | አዘጋጀ |


ምሳሌ:-

1. 


2.





3.




4.




5.



# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ንባብ

## የፆታ እኩልነት



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የፆታ እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል?

ሐ. በቤታችሁ ዉስጥ ምን ምን አይነት ስራ ትሰራላችሁ?

መ. በስራቸው ታዋቂ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላችሁ? ምን ምን ተግባራትን ፈፅመው የታወቁ ናቸው?

የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ አባት፣ እናት እና ሁለት ልጆች በጠዋት ተነስተው ወደሥራ እና ወደትምህርት ቤት ለመሄድ ዝግጅት እያደረጉ ሳለ እናት ወይዘሮ ኤልሳ መጣራት ጀመሩ፡-

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ሰላም ! . . . ሰላም ! . . . ኧረ ሰላም!

ሰላም፡- አቤት እማዬ ምን ሆነሽ ነው?

ወይዘሮ ኤልሳ፡- እኔ ወተቱን እያፈላሁ እና እንዳይገነፍልብኝ

እየጠበኩ ስለሆነ አንቺ የተጣደውን ድስት እንድታማስይልኝ ነው፡፡

ሰላም፡- እማዬ.... የደንብ ልብሴን አለበስኩም፤ ደብተሬንም አላዘጋጀሁም፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ወንድምሽን ጥሪውና ንገሪው ፣ ደብተርሽን አስተካክሎ በቦርሳሽ ውስጥ ያስገባልሽ፡፡

ሰላም፡- እንዴ! እማዬ ኤርሚያስ እንዴት አድርጎ የኔን ደብተር ያስተካክልልኛል? ሁሉንም ደብተሮች እኮ ይዤ አልሄድም፤ በክፍለ ጊዜ መሠረት ዛሬ ምን እንደምንማር እሱ አያውቅም፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ያም ሆነ ይህ ያዘዝኩሽን ሥራ ስሪ፤ ለማዘጋጀቱ እንደሆነ ትደርሺበታለሽ፡፡

አቶ ነብዩ፡- በጠዋት ተነስታችሁ ብትዘገጃጁ ጥሩ ነበር፡፡ ይሄው እኛ ተነስተን ከተቀመጥን እንኳን ስንት ጊዜያችን፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- ወይ ጉድ አንተና ኤርሚያስ ምን ሥራ ትሠራላችሁ፣ በጠዋት ተነስታችሁ የግል ንፅህናችሁን ከጠበቃችሁ በኋላ ልብሳችሁን ለብሳችሁ፣ ቁርስ መብላት ነው፡፡

ሀ. በቤተሰቡ ውስጥ ሥራ እየሠሩ ያሉት እነማን ናቸው?

ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

ኤርሚያስ፡- እማዬ እኔ እኮ እንደ ሰላም ሥራ ላግዝሽ እችል ነበር፤ አባዬና አንቺ ግን ይሄ የሴት ሥራ ነው፤ አንተ ማዕድ ቤት ለማዕድ ቤት ምን ያስኬድሃል እያላችሁ ትገስጹኛላችሁ፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- አዎ ልጄ ጥፋቱ የኔና የአባትህ ነው፡፡ አባትህ በፆታ እኩልነት ለማመን ይቸገራል፡፡ እኔም ብሆን የተለያዩ ሁኔታዎችን ከጎረቤትም ሆነ ከመገናኛ ብዙሃን ባዳምጥም አስተዳደጌ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሮብኛል፡፡

አቶ ነብዩ፡- እኔ የውጭውን ሥራ ስሠራ እውላለሁ፤ አንቺ ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን ሥራ ሰርተሽ ብትጠብቂኝ ምን ችግር አለው?... ሌላው ኤርሚያስ ከትምህርት ቤት እንደተመለስክ የጥናት ሰዓትህን ጠብቀህ እንድታጠና፡፡

ኤርሚያስ፡- አባዬ! . . . ሁልጊዜ እኔን ብቻ አጥና የምትለኝ ለምንድን ነው? ሰላምም ማጥናት አለባት፡፡

ሰላም፡- አዎ እኔን አንድም ቀን አጥኚ ብለኸኝ አታውቅም፡፡

አቶ ነብዩ፡- ልጆቼ የተናገራችሁት ነገር ውስጤን በጣም አስደንግጦታል፡፡ ሁለታችሁንም የምንወዳችሁ ልጆቻችን ናችሁ፡፡ ሰላም የማዕድ ቤት ሥራ እንድትሠራ አንተ ደግሞ እንድታጠና አድልቼ አይደለም፡፡ እናታችሁ ከአንተ ይልቅ ሰላም ሥራ እንድታግዛት ስለምትፈልግ ነው፡፡

ወይዘሮ ኤልሳ፡- እኔ ሰላም እንድታግዘኝ ስለምፈልግ አይደለም፤ ሁልጊዜ የምጠራት፤ በለመድኩትና ባደኩበት ልማድ ውስጥ ስላለሁ ብቻ ነው እንጂ እኔም ሆንኩ ሰላም የማዕድ ቤት ሥራ ብቻ እንድንሠራ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች የሉም፡፡ ሁላችንም ተጋግዘን መሥራት ይገባናል፡፡ ሰላምም እንደ ወንድሟ ትምህርቷን በሚገባ እንድትከታተል እድል ልንሰጣት ይገባል፡፡

ኤርሚያስ፡- ከዚህ በፊት ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ ምን እናድርግ? በሚለው ብንወያይ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ሰላም፡- አዎ ከዚህ በኋላ አባዬ እና ወንድሜ ወጥ መሥራት፣ ቡና ማፍላት፣ ግቢ ማፅዳት፣ አልጋ ማንጠፍና ቤት ማዘጋጀት መልመድ መቻል አለባችሁ፡፡ እኔ ወንድሜን አለማምደዋለሁ፤ እማዬ ደግሞ አባዬን አለማምጂው፡፡ ከዚህ በኋላ ዕቅድ አውጥተን ሥራችንን እንሥራ፡፡

ቤተሰቡ በሙሉ በሰላም ሐሳብ በመስማማት በቤት ውስጥ የሥራ ክፍፍል ዕቅድ በማውጣት እና በዕቅዳቸው መሠረት በመሥራት በቤታቸው ውጤታማ የሆነ የሥርዓተ-ጾታ አመለካከት እንዲኖር ማድረግ ቻሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

ሀ. "የጾታ እኩልነት " በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሠረት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ወይዘሮ ኤልሳ ሰላምን የጠሯት ለምንድን ነው?
2. የእነ አቶ ነብዩ ቤተሰብ ከአጉል ልማድ እንዴት መላቀቅ ቻለ?
3. የሰላም ቤተሰቦች በሰላም ላይ ያሳደሩት አሉታዊ ተፅዕኖ ምን ነበር?
4. ቤተሰቡ እየተወያየ የነበረው በየትኛው ጊዜ ነው?
5. ጎረቤቶቻቸው ስለ ሥርዓተ-ጾታ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ✍ ጽሕፈት

ሀ. "የጾታ እኩልነት " በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ሥራን ተከፋፍሎ መሥራት ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
2. ሥርዓተ-ጾታ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የጭውውቱ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

### ቃላት

ሀ. "የጾታ እኩልነት " በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ገነፈለ = ፈሰሰ

1. መርሀ-ግብር
2. መገሰጽ
3. መቸገር
4. ተጽዕኖ
5. መወያየት
6. አመለካከት
7. ማገዝ
8. ማለማመድ

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## መናገር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ እና የመከራከሪያ ርዕስ መሠረት አስፈላጊዊውን መረጃ በመሰብሰብ እንዲሁም ዳኛ በመምረጥ ክርክር አቅርቡ።

የክርክር ርዕስ

በቤት ውስጥ የወንዶች እና የሴቶች ሚና ምን መሆን አለበት?

## ጽሕፈት

ሀ. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል እና ቃላቱን በማስማማት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

1. የታሸው ዳማከሴ ትንሽ እንዲቆይ አደረጉ።
2. ዮሴፍ ቆሻሻ ሸተተው።
3. ዳማከሴ ቆርጠው በመዳፋቸው አሹ።
4. እናቱ በጣም ተጨነቁ።
5. እራሱን አመመው።

6 የእራስ ምታቱም ቀነሰለት።

7. በግማሽ ማንኪያ አድርገው አጠጡት።

ለ. የሚከተለውን የቀለሞች ፍንጭ እንደአቀማመጣቸው በመከተል ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ ያሉትን ቃላት በቅደም ተከተላቸው በማገጣጠም አንቀጽ ጻፉ።

የቀለሞች ፍንጭ:-

መነሻ ቀለም:- ቢጫ

ማጠናቀቂያ ቀለም:- ብርቱካናማ

| 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንሳት ይቻላል:: | አባባል | የሚለውን | ናት::" | ልጅ |
| → ሴቶች | የማንናዘብ | ችሎታቸውም | ብልህ | "ሴት |
| አሳቸው:: | ለአገር | ዘንድ | ከፍተኛ | ለዚህም |
| ጥበብም | በማህበረሰቡ | ባለውለታዎች | ይታወቃል:: | ነው:: |
| ብልሃትና | ጥንካሬያቸውም | አስተሳሰባቸውም | ናቸው:: | ከችሎልነት |
| ነው:: | ብሩህ | ይመርጣሉ:: | መፈጋገት | ይልቅ |

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## 🎓 ሰዋስው

ሀ. በምሳሌው መሠረት በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ለይታችሁ ጻፉ::

ምሳሌ:- እስማኤል አንደኛ ስለወጣ ተደሰተ:: ተደሰተ

1. በርናባስ ወደትምህርት ቤት ሄደ::
2. ናሆም በጥሩ ስነ-ምግባር ታነፀ::
3. የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር ለተማሪዎች ምክር ሰጡ::
4. ሂክማ ባሳየችው ጥሩ ባህሪ ተሸለመች::
5. በአገራችን ለባህላዊ ሕክምና የሚያገለግሉ በርካታ ዕፀዋት ይገኛሉ::
6. የገዳ ስርዓት አንዱ የዲሞክራሲ መገለጫ ነው::
7. ኢትዮጵያ በርካታ ቅርሶችን በዮኔስኮ አስመዝግባለች::
8. የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ሽምግልና ተቀመጡ::

9. ሴቶች በከፍተኛ የአመራርነት ደረጃ ላይ አገለገሉ።

10. የህዳሴው ግድብ ሁለተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ተጠናቀቀ።

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ስም የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ።

1. ትልቅ ዳቦ በላሁ።
2. መፅሃፍ ተገዛልኝ።
3. አልማዝ ጎበዝ ናት።
4. ጥቁር ጫማ አለኝ።
5. አዲስ አበባ ታምራለች።

## ጽሕፈት

ሐ. በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙትን ግሶች ብቻ በመለየት ጻፉ፡ .





ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ የተጣለው መጋቢት 24/ 2003 ዓ.ም ነው። ግድቡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ልዩ ስሙ ጉባ በተባለ ወረዳ ይገኛል። ግድቡ በኢትዮጵያዊያን ዕውቀት፣ ገንዘብ እና ጉልበት የሚሠራ ሲሆን ሲጠናቀቅም 6,450 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጫል። ይህም ኃይል የኢትዮጵያዊያንን ሁለንተናዊ ችግሮች ይፈታል። በመሆኑም ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ኩራትና የጀግንነታችን መገለጫ የሆነ የዚህ ትውልድ አሻራ ነው። ስለዚህ ግድቡን ለማጠናቀቅ እኛ

ኢትዮጵያዊያን በአንድነት ልንረባረብ ይገባል፡፡

መ. በምሳሌ መሠረት የተሰጧችሁን ግሶች  ወደ ስም ቀይራችሁ ፃፉ፡፡

| ተ.ቁ | ግስ | ስም |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ዘነበ | ዝናብ |
| 1 | ዘፈነ | |
| 2 | ተማረ | |
| 3 | ቀለደ | |
| 4 | ሠራ | |
| 5 | ጨፈረ | |

ሠ. በሚከተለው ምሳሌ መሠረት በተሰጡት ግሶች  ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡ ፡

ምሳሌ፡-   ሠራ  - ምንተስኖት የቤት ሥራውን በወቅቱ ሠራ፡፡

1. መነዘረ
2. ተናገረ
3. መጣ
4. ጨመረ
5. ገመገመ
6. ወደደ

# የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች

## 1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው አጭር መልስ ስጡ፡፡

ሀ. የውሰት ቃለትን በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

ለ. ስም ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. አከናወነ፣ አለ፣ ናቸው ተሰበረ በሚሉ ግሶች ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

# ምዕራፍ 5

# ጉብኝት

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስለጉብኝት መዳረሻዎች ያዳመጣችሁትን በቃላችሁ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- ምንባብ አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአንቀጽ ባህሪያትን ትለያላችሁ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍ ተነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም ዓረፍ ተነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

## በደቡብ ክልል የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች





ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ፎቶግራፉን ስትመለከቱ ምን ተረዳችሁ?

ሐ. ለታሪካዊ ቅርሶች ምን አይነት ጥበቃ መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. "የደቡብ ክልል የቱሪስት መስህቦች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ምንባብ ባዳመጣችሁት መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. በደቡብ ክልል የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ማን ማን ናቸው?
2. የጥያ ትክል ድንጋይ የሚገኘው የት አካባቢ ነው?
3. የተፈጥሮ መስህቦቻችንን ለመጠበቅ ምን መደረግ አለበት?
4. ጎብኚዎች እንዲጎበኙ የማስተዋወቅ ሥራ ከማን ይጠበቃል?
5. የተፈጥሮ መስህቦች የገቢ ምንጭ ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. "በደቡብ ክልል የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ምንባብ ባዳመጣችሁት መሠረት የሚከተሉት ቃላት የያዙትን አውዳዊ ፍች በቃላችሁ አብራሩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ፓርክ | 4. ማዕከል |
| 2. ቱሪስት | 5. ጥቅም |
| 3. ተፈጥሯዊ | 6. እርከን |

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. በርካታ | 3. ከስር | 5. ወርደው |

2. ሰፊ 4. የተለየ 6. ጨለማ

ሐ. ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት የያዙት ሐሳብ ትርጉም የሚሰጠው በማጥበቅ ወይንም በማላላት ሲነበብ መሆኑን ለዩ።

ምሳሌ፡- አለኝ

የአማርኛ መጽሐፍ አለኝ። ጠብቆ

እመጣለሁ አለኝ። ላልቶ

1. በዓለም ላይ ረጅሙ ወንዝ የኢትዮጵያው አባይ ወንዝ ነው።

የሰው ልጅ በባህሪው አባይ መሆን የለበትም።

2. በተናገረኝ መጥፎ ነገር ሣር ከምውል መከርኩት።

የመናፈሻ ቦታው ሣር ለብሷል።

3. በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አማኝ አለ።

ጓደኛዬ በሌለሁበት አማኝ።

5. ከስፖርት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ውሃ ዋና ነው።

ጡሜቦ የትምህርት ቤታችን ዋና ርዕሰ መምህር ነው።

6. በደቡብ ክልል ውስጥ ሰባ ትምህርት ቤቶች ተመረጡ።

በሬው በሚገባ ስለተቀለበ ሰባ።

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### ጽሕፈት

ሀ. በምሳሌው መሠረት የሚከተሉት ቃላት በማጥበቅ እና በማላላት ስናነባቸው የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

1. የተበላሸ ቲማቲም በሽታ ይታወቃል።

("በሽታ" የሚለው ቃል በዚህ ዓረፍነገር ውስጥ የምናነበው በማጥበቅ ነው።)

በዚህ ዓረፍተ ነገር መሠረት ትርጉሙ የሚፈጥረው መጥፎ ጠረን የሚል ይሆናል።

2. ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ሰዎችን የሚያጠቃ በሽታ ነው።

("በሽታ" የሚለው ቃል በዚህ ዓረፍ ተነገር ውስጥ የምናነበው በማላላት ነው።

በዚህ ዓረፍተ ነገር መሠረት ትርጉሙ ሕመም የሚል ይሆናል።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ቀናት | 3. ለጋ | 5. ጥልቅ |
| 2. አያት | 4. ያነባል | |

ለ. ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተነገር መስርቱ።

| | |
|---|---|
| 1. ታነጸ | 5. ታሪካዊ |
| 2. አጌጠ | 6. ተሳታፊ |
| 3. ስልጣኔ | 7. ድንቅ |
| 4. የተለየ | 8. ውበት |

ሐ. "የደቡብ ክልል የቱሪስት መስህቦች" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን የምንባብ ሐሳብ በአራት ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

### አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም



የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም



የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም



የፖስታ ሙዚየም

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ቤተ-መዘክር ወይም ሙዚየም ማለት ምን ማለት ይመስላችል?

ለ. ፎቶዎቹን በማየት ምንባቡ ምን ሊነግራችሁ እንደሚችል ገምቱ?

ሐ. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የምታውቋቸውን የጉብኝት ስፍራዎች ዘርዝሩ?

በአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ተሰባስበው የሚገኙባቸው አሥራ አምስት ሙዚየሞች አሉ፡፡
እነዚህም፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም፣ የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም፣ አዲስ አበባ ሙዚየም፣ የርዕሰ አድባራት እንጦጦ ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ሙዚየም፣ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ሙዚየም፣ የመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሙዚየም፣ የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሙዚየም፣ የታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ቤተክርስትያን ሙዚየም፣ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ሙዚየም፣ የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስትያን ሙዚየም፣ መንበረ ፓትርያርክ ቤተ-መጻሕፍት ሙዚየም፣ የስፖርት ሙዚየም ጃንሜዳ፣ የነገሥታት ባቡሮች ሙዚየም - ለገሃር ባቡር ጣቢያ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አሥራ አምስት ሙዚየሞች ውስጥ አራቱን እናስተዋውቃችሁ፡፡

ሀ. ከላይ ከተጠቀሱት ሙዚየሞች ውስጥ እናንተ የትኛውን ለመጎብኘት ትፈልጋላችሁ?

ለ. ከላይ ከተጠቀሱት ሙዚየሞች ምንባቡ የትኞቹን ሊያስተዋውቃችሁ እንደሚችል ገምቱ?

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ነው፡፡ ይህም በ1936ዓ.ም መጨረሻ የተመሠረተ ሲሆን በውስጡ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህም ክፍሎች የቅርስ ጥበቃ፣ የመረጃ እንዲሁም የአውደ ርዕይ ክፍሎች ይባላሉ፡፡ በሙዚየሙ ውስጥ የአርኪዮሎጂ፣ የጥንታዊና የመካከለኛ ዘመን ቅርሶች፣ የሰዎች ጥበባዊ የፈጠራ ሥራ እንዲሁም የተለያዩ ብሔረሰቦች ባህላዊ ቁሳቁሶች ይገኛሉ፡፡

ጠሁለተኛው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም ነው፡፡ ይህ ሙዚየም በፊት ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በሚባለውና የአጼ ኃይለሥላሴ ቤተ-መንግሥት በነበረው፣ አሁን ደግሞ 6ኪሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተብሎ በሚታወቀው ግቢ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ይህኛው ደግሞ ስለኢትዮጵያ የተሠሩ የጽሑፍ ሥራዎችንና በኢትዮጵያ ያሉ ብሔረሰቦች ባህልና ታሪክ የሚያሳዩ መረጃዎች የተሰባሰቡበት ነው፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ ቤተ-መጻሕፍትም ይገኝበታል፡፡

ሦስተኛው የምናስተዋውቃችሁ አራትኪሎ የሚገኘው የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም ይባላል:: በዚህ ሙዚየም ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው የዱር እንስሳት፣ አእዋፋት፣ የውሃ ውስጥ ፍጥረታት ይገኛሉ:: የሚገርማችሁ በዚህ ሙዚየም ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እንስሳትንም ለማየት ትችላላችሁ:: ይህ ሙዚየም በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው የዱር እንስሳት፣ የአእዋፋትና የውሃ ውስጥ ፍጥረታት ለእይታ ቀርበው የሚገኙበት ነው:: በሙዚየሙ ከሦስት ሺህ አምስት መቶ በላይ የተለያየ ዓይነት እንስሳትና ከአንድ ሺህ አንድ መቶ በላይ የእንስሳት ዝርያዎች ይገኛሉ::

የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም ሌላውና አራተኛው የምናስተዋውቃችሁ ሙዚየም ነው:: ይህ ሙዚየም በዓለማችን ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የታተሙና በዓለም ፖስታ አባል አገራት የሚላኩ ቴምብሮች ተሰባስበው ለእይታ የሚቀርቡበት ነው:: ቴምብሮቹ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ ውብ የተፈጥሮ መስህቦችን፣ የብሔረሰቦችን ባህል፣ የታዋቂ ሰዎችን፣ የዕፀዋትንና የአእዋፍን ብሎም የእንስሳትን ምስል የሚያሳዩ ናቸው:: እነዚህ ቴምብሮች በፖስታ ላይ ተለጥፈው በዓለም አገራት ሲዞሩ አገራችንን ያስተዋውቃሉ:: ሙዚየሞችን መጎብኘት የአገር ታሪክ፣ የጀግኖችን ገድልና ሥራ፣ ባህል፣ ቅርስ . . . እንድናውቅ ያደርጋል:: እናንተም ያስተዋወቅናችሁንና የቀሩትን ሙዚየሞች በተገኘው አጋጣሚ ጎብኙ እንላለን::

(ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ፤ 78ኛ ዓመት፤ ቁጥር181፤ መጋቢት 1 ቀን 2011ዓ.ም፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታትሞ፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ)

## መናገር

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች "አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)" በሚለው ምንባብ መሠረት የያዙት ሐሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ከምንባቡ ማስረጃ በማቅረብ በቃል አብራሩ::

1. ሙዚየሞች የአንድን አገር ባህልና ታሪክ መገለጫ ቅርሶችን የሚይዙ የጉብኝት ቦታዎች ናቸው::
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ቀደም ሲል ገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት

በመባል ይታወቅ ነበር፡፡

3. ብዙ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሳትና አዕዋፋት የሚገኙት በተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ነው፡፡

4. በፖስታ ላይ የሚለጠፉ ቴምብሮች ፋይዳቸው አገራችንን ለዓለም አገራት ማስተዋወቅ ነው፡፡

5. ሙዚየም መጎብኘት ከመዝናኛነት ያለፈ ጥቅም የለውም፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

ሀ. ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በምንባቡ መሠረት ስጡ፡፡

1. ታሪካዊ
2. ምስል
3. ገድል
4. መለጠፍ
5. ጥበቃ

ለ. ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በምንባቡ መሠረት ስጡ፡፡

1. ውብ
2. መሰረተ
3. ተፈጥሯዊ
4. ቀረበ
5. ፈጠራ

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ጽሕፈት

ሀ. በ"ሀ" ረድፍ ለተደረደሩ የሙዚየም መግለጫዎች ከ"ለ" ረድፍ ከተዘረዘሩ የሙዚየም ዓይነቶች ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. የታተሙና በዓለም አገራት የሚላኩ ቴምብሮች ተሰባስበው የሚገኙበት፤ | ሀ. የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ሙዚየም |
| 2.የዱር እንስሳት፣አዕዋፋትና የውሃ ውስጥ ፍጥረታት የሚገኙበት፤ | ለ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም |
| 3. ስ ለኢትዮጵያ የተጻፉ የጽሑፍ ሥራዎችና ቤተ-መጽሐፍ የሚገኝበት፤ | ሐ. የኢትዮጵያ ፖስታ ሙዚየም |
| 4. ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት፤ | መ. የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም |

## ቃላት

ለ. በሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹ የተሟላ ሐሳብ እንዲሰጡ አድርጉ።

| ብርቅዬ | ቴምብር | ቤተ-መዘክሮች | ቅርሶች | መጎብኘት |
|---|---|---|---|---|

1. ሙዚየም ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ________የሚገኙበት ስፍራ ነው።
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ እንስሳት____________እንስሳት ይባላሉ።
3. ———በፖስታ ላይ የሚለጠፍ አገርን የሚያስተዋውቅ ሕጋዊ ማረጋገጫ ነው።

4. ቤተ-መዘክሮችን__________አገርን ማወቅ ነው፡፡

5. ቅርሶች በሚገባ ተጠብቀው እንዲቆዩ________ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

### ሐ. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

1. ቅርስ
2. ብሔራዊ
3. ፍጥረት
4. እይታ
5. መስህብ
6. ባህል
7. ፈጠራ

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

# አቀላጥፎ ማንበብ

### መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡



# ደቡብ ክልል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል በኢትዮጵያ ከሚገኙ አስራ አንድ ክልሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ 105,887.18 ካሬ ኪ.ሜ ቦታ የሚሸፍን ሲሆን በምስራቅ ሲዳማ፣ በምዕራብ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ምዕራብ ከደቡብ ሱዳን፣ በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ከኦሮሚያ፣ በደቡብ ከኬንያ ጋር ይዋሰናል፡፡ ክልሉ ብዙ ከተሞች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል አርባ ምንጭ፣ ሶዶ፣ ሆሳዕና፣ ሀላባ፣ ዲላ፣ ጂንካ፣ ወልቂጤ፣ ወዘተ. ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ክልሉ በ11 ዞኖችና በ6 ልዩ ወረዳዎች የተዋቀረ ሲሆን በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መሠረት ወደ 15,042,531 የሚጠጋ ሕዝብ የሚገኝበት ሲሆን ይህም ከአገሪቱ ሕዝብ 20.4% ይሸፍናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ 55 ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚኖሩ ሲሆን የእነዚህም ቋንቋዎች በአፍሮ እስያዊ (ኩሻዊ፣ ኦሞአዊ እና ሴማዊ) ንዑስ ክፍሎችን ጨምሮ ናይሎ ሳሃራዊ የቋንቋ ቤተሰቦች ይመደባሉ፡፡ ክልሉ 4270 ሜትር ከፍታ ካለው በጋሞና በጎፋ መካከል የሚገኘው የጉጌ ተራራ እስከ 376 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ ከፍታ ያለው የደቡብ ኦሞው ጨልባና ቱርካና ሐይቅ አካባቢ ያለውን ዝቅተኛ ቦታ ጨምሮ በርካታ የተለያየ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥን ይዟል፡፡ ክልሉ በሀሩር፣ በቆላ፣ ወይና ደጋና ደጋ የአየር ንብረት የተከፋፈለ ሲሆን ለእርሻ፣ ለከብት እርባታ ምቹ የሆነና በደንም የተሸፈነ ክልል ነው፡፡ በተጨማሪየአባያ፣የጫሞ፣የጨውባህርናቱርካናየመሳሰሉሐይቆችየኦሞናጎጀብ ወንዞች ባለቤት ከገናሌ እስከ ዳዋ፣ ከባሮ እስከ አኮቦ፣ ከኦሞ እስከ ጊቤ በአጠቃላይ 32% የሚደረሱ ተፋሰሶችን ይጋራል፡፡ የአጀራና ጋቺቴ ፏፏቴዎች፣ የነጭ ሣር፣ ኦሞ ማዜና የማጎና የጨበራ ጩጩራ ብሔራዊ ፓርኮች የሚገኙበት ነው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስምንት

### ጽሕፈት

ምሳሌ:

1. የደንብ ልብሱን ቀየረ፡፡

2. ምንተስኖት 10:00 ሰአት ሲሆን ከትምህርት ቤት ተመለሰ፡፡
3. በመጨረሻም ከእህቱ ጋር በመሆን የግቢያቸውን አትክልት ውሃ አጠጣ፡፡
4. የተሰጡትን የቤት ሥራዎች ሰርቶ ጥናቱን አጠና፡፡
5. ጥቂት ረፍት አደረገ፡፡

ምንተስኖት 10:00 ሰአት ሲሆን ከትምህርት ቤት ወደቤት ተመለሰ፡፡ ቤት እንደደረሰም የደንብ ልብሱን ቀይሮ ጥቂት ረፍት ካደረገ በኋላ የተሰጡትን የቤት ሥራዎች ሰርቶ ጥናቱን አጠና፡፡ በመጨረሻም ከእህቱ ጋር በመሆን የግቢያቸውን አትክልት ውሃ አጠጣ፡፡

ሀ. ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ጓደኛዋ ቀስበቀስ የምልክት ቋንቋውን አለማመደቻት፡፡
2. የምልክት ቋንቋ የምትችለው ጓደኛዋ እንድታለማምዳት ጠየቀቻት፡፡
3. በዚህም ደስተኛ ሆነች፡፡
4. ዓይናለም የምልክት ቋንቋ ለመልመድ ትፈልጋለች፡፡
5. ዓይናለም በአጭር ጊዜ የምልክት ቋንቋ መጠቀም ቻለች፡፡

ለ. በትምህርት ቀናችሁ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከገባችሁበት ሰዓት አንስቶ እስከ እረፍት ሰዓት ድረስ የሠራችሁትን ዋና ዋና ተግባር የአንቀጽ ባህርያትን በመጠበቅ በአንድ አንቀፅ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ሰዋስው

### ገላጭ ቃላት

ሀ. በዝርዝር ለተቀመጡ ገላጭ ቃላት ምላሽ የሚሆኑ የገላጭ ቃላት ዓይነቶችን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መጠን | ቀለም | ወገነ |
| ብዛት | ባህሪ | ቅርጽ |

1. አረንጓዴ፣ ጥቁር፣ ሰማያዊ፣ ነጭ ..
2. አያሌ ፣ ሺህ ፣ ብዙ ፣ አንድ . . .
3. ክፉ ፣ ደግ ፣ የዋህ ፣ ጥሩ . . .
4. ኢትዮጵያዊ፣ ኤርትራዊ፣ ኬንያዊ...
5. ክብ ፣ ሞላላ ፣ ጥምዝ ፣ሾጣጣ ..
6. አጭር፣ ወፍራም ፣ቀጭን፣ ረጅም..

ለ. በምሳሌው መሠረት በክፍት ቦታው ላይ ተገቢውን ገላጭ ቃል በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡

ምሳሌ፡- <u>ታታሪ</u> ሰው እወዳለሁ፡፡

1. __________መጽሐፍ ተቀደደ፡፡
2. አባቴ __________ቦርሳ ገዛልኝ፡፡
3. ወንድሜ__________ቤት ሠራ፡፡
4. ዛፉ__________ነው፡፡
5. ትምህርት ቤታችን______________ነው፡፡

## ሐ. በምሳሌው መሠረት በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ገላጭ ቃላት በመለየት ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ዓለማችን ሞላላ ቅርጽ አላት፡፡ ሞላላ

1. ቸር ሰው ያለውን ያካፍላል፡፡
2. በርካታ ህዝብ በተገኘበት የጊፋታ በዓል ተከበረ፡፡
3. ኢትዮጵያዊ አለባበሳችን ያምራል፡፡
4. ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ትልቅ ግድብ ገነባች፡፡
5. ነጭ በትር (ኋይት ኬን) የዓይነ-ስውር መሪ ነው፡፡

## መ. የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት በየምድባቸው ስር አስቀምጡ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያዊ | ግራጫ | በርካታ | ክብ | ቢጫ | ዝርግ |
| ጥቂት | ሩህሩህ | ሰፊ | የዋህ | አነስተኛ | ሱዳናዊ |
| ሦስት | ማዕዘን | ኤርትራዊ | ጥቁር | ጠባብ | ቀጭን |
| አዛኝ | ወይንጠጅ | ቸር | ትልቅ | ኬኒያዊ | ጠፍጣፋ |
| ብዙ | | | | | |

**መጠን**

1.
2.
3.
.

**ቅርጽ**

1.
2.
3.
4.

**ባህሪ**

1.
2.
3.
.

**ወገን**

1.
2.
3.

**ቀለም**

1.
2.
3.
4.

**ብዛት**

1.
2.
3.
4.

### ሠ. በምሳሌው መሠረት የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- አያሌ - በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አያሌ ህዝብ ተሳተፈ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ቀይ | 3. ቻይናዊ | 5. ሩህሩህ |
| 2. መጥፎ | 4. አጭር | |

# የምዕራፍ አምስትየክለሳ ጥያቄዎች

1. የአንቀጽ ባህርያትን በዝርዝር አስረዱ።

2. ገላጭ ቃል ማለት ምን ማለት ነው?

3. የሚከተሉትን ገላጭ ቃላት ዓይነታቸውን ግለፁ። በመቀጠል ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

- አዲስ
- ድቡልቡል
- አዛኝ
- ወርቃማ
- ጥቂት

4. በደቡብ ክልል ውስጥ ከጎበኛችሁት ስፍራ ውስጥ ወይም ከጎበኙ ሰዎች በመጠየቅ እጅግ ስለማረካችሁ ቦታ የአንቀጽ ባህርያትን ያሟላ አንድ አንቀጽ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

# ምዕራፍ 6

# ስፖርት

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስለአዳመጣችሁት ነገር በቃላችሁ ሃሳብለዋወጣላችሁ፡፡
- እያንዳንዱን አንቀጽ አንብባችሁ ከጽሁፉ ውስጥ ያገኛችሁትን ሃሳብ ታብራራላችሁ፡፡
- የቃላት እውቀታችሁን ታሳድጋላችሁ፡፡
- ባለቤትና ግስን አስማምታችሁ አረፍተነገር ቅራላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

### የኦሎምፒክ ወርቆች





## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. የምትመለከቷቸው ፎቶግራፎች የነማን ናቸው?

ለአገራቸው ምን እንዳበረከቱስ ታውቃላችሁ?

ሐ. የምታውቋቸውን የስፖርት ዓይነቶች ተናገሩ?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. “የኦሎምፒክ ወርቆች” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. በተከታታይ የሮም እና የቶኪዮ የኦሎምፒክ ማራቶን ውድድሮችን ያሸነፈው አትሌት ማን ይባላል?
2. በስሟ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰየመላት አትሌት ማን ትባላለች?
3. “ኢትዮጵያ የሌለችበት ኦሎምፒክ አይደምቅም!” የተባለው ለምንድን ነው?
4. ኃይሌ ገብረስላሴ ተደጋጋሚ ድሎችን እንዲያስመዘግብ የገፋፋው ምንድን ነው?

## ለ. “የኦሎምፒክ ወርቆች” በሚለው ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ አትሌት ማን ናት?

   ሀ. ጥሩነሽ ዲባባ　　ሐ. መሠረት ደፋር

   ለ. ደራርቱ ቱሉ　　መ. እጅጋየሁ ዲባባ

2. ብራዚል በዓለም ዋንጫ ተሳትፎ ስትታወቅ ኢትዮጵያ ደግሞ በ______ ተሳትፎ ትታወቃለች።

   ሀ. በኦሎምፒክ　　ሐ. በዝላይ

   ለ. በአፍሪካ ዋንጫ　　መ. በወርቅ ሜዳሊያ

3. በአንድ የኦሎምፒክ መድረክ ድርብ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት መሆንን ለዓለም ያስተማረው አትሌት ማን ነው?

   ሀ. ኃይሌ ገ/ስላሴ　　ሐ. ምሩፅ ይፍጠር

   ለ. አበበ ቢቂላ　　መ. ቀነኒሳ በቀለ

4. በስሟ ሆስፒታል የተሰየመላት አትሌት ማን ናት?

   ሀ. መሠረት ደፋር　　ሐ. ፋጡማ ሮባ

   ለ. ደራርቱ ቱሉ　　መ. ጥሩነሽ ዲባባ

5. በአቴንስ ኦሎምፒክ በ5ሺ. ሜትር 1ኛ በመሆን ወርቅ የተሸለመች አትሌት ማን ናት?

   ሀ. መሠረት ደፋር　　ሐ. ደራርቱ ቱሉ

   ለ. ጥሩነሽ ዲባባ　　መ. ብርሃኔ ሀደሬ

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. “የኦሎምፒክ ወርቆች” በሚለው ምንባብ መሠረት በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ፈፀመ | ሀ. አጋጣሚ |
| 2. ውድድር | ለ. እጥፍ |
| 3. ድርብ | ሐ. ፉክክር |
| 4. ዕድል | መ. ጀግና |
| 5. ጀብደኛ | ሠ. አከናወነ |

ለ.“የኦሎምፒክ ወርቆች” በሚለው ምንባብ መሠረት በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡


| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ድል | ሀ. ጨረሰ |
| 2. በረታ | ለ. ተቀጣ |
| 3. ተሸለመ | ሐ. ዘገየ |
| 4. ፈጠነ | መ. ሽንፈት |
| 5. ጀመረ | ሠ. ደከመ |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት


## ሰዋስው


ሀ. በምሳሌው መሠረት ዋናውን ቃል ከቅጥያዎች ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃል መስርቱ፡፡


ምሳሌ፡-






1. አባትነት
2. አባታዊ
3. አባቶች

1.



2.



3.



4.



5.


ለ. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከተዘረዘሩት ቃላት ጋር በማገናኘት ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ፡፡

(ቅጥያዎችን ከአንድ ጊዜ በላይ መድገም ይቻላል፤ ለአንድም ቃል ከአንድ በላይ ቅጥያ መጠቀም ይቻላል፡፡)

| | | |
|---|---|---|
| - ኣማ | - ነት | - ኦች |
| - ኣዊ | - ዎች | - ኧ ኛ |

ምሳሌ፡- ሀ. የዋህ = የዋህነት ፣ የዋሆች

ለ. አገር = አገራዊ ፣ አገሮች ፣ አገርኛ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ደግ | 4. ድመት | 7. በጎ | 10. ሰማይ |
| 2. አሸዋ | 5. ኢትዮጵያ | 8. ተራራ | |
| 3. ነገር | 6. ጫማ | 9. ተንኮል | |

## ጽሕፈት

ሀ. ከዚህ በታች በተሰጧችሁ ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ታዋቂ | 3. ማስመዝገብ | 5. መገፋፋት |
| 2. ጥርጥር | 4. አክብሮት | 6. አስደናቂ |

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

# የኢትዮጵያ የስፖርት አባት




## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችል?

ለ. የምትመለከቱት ፎቶግራፍ የማን ይመስላችኋል?

ሐ. ፎቶውን በማየት ምንባቡ ምን ሊነግራችሁ እንደሚችል ገምቱ?

አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከእናታቸው ወይዘሮ ሙላቷ ገብረ ሥላሴ እና ከአባታቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ መስከረም 1 ቀን 1914 ዓ.ም ተወለዱ:: አቶ ይድነቃቸው እንደማንኛውም የዘመኑ ልጆች እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቄስ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት ተምረዋል:: በመቀጠልም የፈረንሳይኛ ትምህርትን ደግሞ በአሊያንስ፣ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል::

በወቅቱም ለእግር ኳስ፣ ለብስክሌትና ለሩጫ ስፖርቶች ልዩ ፍቅር ነበራቸው:: ብስክሌቱንና ሩጫውን ባይገፉበትም እግር ኳሱን ግን በተጫዋችነት፣ በአሰልጣኝነትና በኋላም በአመራርነት እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ቀጥለውበት ዛሬም ድረስ ስማቸውን ማስጠራት የቻሉበት ስፖርት ሆኖላቸዋል::

ገና በስምንት ዓመታቸው የትምህርት ቤቱ የሕፃናት እግር ኳስ ቡድንን

በአምበልነት እየመሩ ተጫውተዋል፡፡ በ1924 ዓ.ም ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና የስዊድኑ ንጉሥ ልጅ በተገኙበት መድረክ ይድነቃቸውና የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው የስፖርት ትርዒት አቅርበው ሽልማት ተቀብለዋል፡፡ በስምንት ዓመት እድሜያቸው የስፖርት ዓለም ተሳትፎን የጀመሩት ይድነቃቸው፣ በ14 ዓመታቸው የዛሬውን ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ቡድንን ተቀላቀሉ፡፡

ይድነቃቸው ለ23 ዓመታት ያህል ለቅዱስ ጊዮርጊስ በመጫወት እስካሁን ድረስ ባለክብረወሰን ናቸው፡፡ ይድነቃቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ በቆዩባቸው ዓመታት ከተጫዋችነት በተጨማሪ አሰልጣኝ ሆነውም አገልግለዋል፡፡ በአንድ የውድድር ዘመን ለክለቡ 43 ግቦችን ማስቆጠር ችለዋል፡፡ ይህ ስኬትም ይድነቃቸውን እስካሁን ድረስ ባለክብረወሰን አድርጓቸዋል፡፡ የተጫዋችነት ዘመናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አሰልጣኝነት በመሸጋገር የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድንን መርተዋል፡፡ ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ አንድ ለእናቱ የሆነውን የአፍሪካ ዋንጫዋን በ1954 ዓ/ም ስታሸንፍ የቡድኑ አሰልጣኝ ይድነቃቸው ተሰማ ነበሩ፡፡

ሀ. በስንት ዓመታቸው ስፖርት ጀመሩ? የት እና በምን የስፖርት ዓይነት?

ለ. አቶ ይድነቃቸው ከእግር ኳስ ተጫዋችነት እና ከአሰልጣኝነት ሌላ ምን የሰሩ ይመስላችኋል?

አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከተጫዋችነትና ከአሰልጣኝነታቸው ባሻገር ታላላቅ ተግባራትን ያከናወኑትና ታዋቂነትን ያተረፉት የስፖርት ማኅበራትን በማደራጀትና በመምራት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ስፖርት ጽሕፈት ቤትን አቋቁመው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ጥረዋል፡፡ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ሲመሠረትም አስተዋጿቸው እጅግ የጎላ ነበር፡፡ አቶ ይድነቃቸው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ እና የካፍ ፕሬዝደንት ሆነው ተሹመው አገልግለዋል፡፡ የበርካታ ሪከርዶች ባለቤት የሆኑት አቶ ይድነቃቸው፤ ከውጭ ሀገራት መንግሥታት ሳይቀር ብዙ ዋንጫዎችን፣ሜዳሊያዎችንና ሌሎች ሽልማቶችን አግኝተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ዘመናዊ የስፖርት አባት በመባል የሚታወቁት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ነሐሴ 13 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

(ምንጭ፡- አዲስ ዘመን 79ኛ ዓመት ቁጥር 217፤ 2012ዓ.ም፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተጣጥሞ የተወሰደ)

# ተግባር አንድ:- አንብቦ መረዳት

ሀ. “የኢትዮጵያ የስፓርት አባት” በሚለው ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በስንት ዓመተ ምህረት ተወለዱ?
2. ምንባቡ ስንት አንቀጾች አሉት?
3. ከእግር ኳስ ተጫዋችነት በተጨማሪ በምን፤ በምን ኃላፊነት ላይ እንደሰሩ ዘርዝሩ?
4. አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ቡድን እስከ ስንት ዓመታቸው ድረስ ተጫወቱ?
5. በስንት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ?

## ቃላት

ሀ. በምሳሌው መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ።

| | ቃላት | ተመሳሳይ ፍች | ተቃራኒ ፍች |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ | አሸነፈ | ድል አደረገ | ተረታ |
| 1 | ሁልጊዜ | | |
| 2 | መፈለግ | | |
| 3 | በፊት | | |
| 4 | መዘዋወር | | |
| 5 | ማግኘት | | |
| 6 | ውጤት | | |

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቻቸውን ምረጡ፡፡

1. እኛ ተማሪዎች ጥሩ <u>ባህሪ</u> ልናዳብር ይገባል፡፡

ሀ. ጠባይ ሐ. ባህል

ለ. ጎበዝ መ. ልምድ

2. በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ትምህርታዊ <u>ውድድር</u> ያስደስታል፡፡

ሀ. ሩጫ ሐ. ፉክክር

ለ. መዋደድ መ. መውደድ

3. ኢትዮጵያ የሰው ዘር <u>ማዕከል</u> ናት፡፡

ሀ. እናት ሐ. አዋቂ

ለ. ዓይነት መ. መገኛ

4. ሰዎች በመልካም ሥራቸው ሲመሰገኑ በመጥፎ ተግባራቸው ደግሞ <u>ይኮነናሉ</u>፡፡

ሀ. ይናዘዛሉ ሐ. ይሸለማሉ

ለ. ይወገዛሉ መ. ይሾማሉ

5. <u>ባለንጀራን</u> እንደራስ መውደድ ይገባል፡

ሀ. ቤተሰብን ሐ. ጓደኛን

ለ. ዘመድን መ. ጎረቤትን

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## 📖 አቀላጥፎ ማንበብ

*መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡*

### አንድ ብልህ ዐይነ-ስውር

አንድ ዐይነ-ስውር ገንዘብ አጠራቅሞ ማስቀመጫ ስላጣ አንድ ቀን በሌሊት ተነሳና በከረጢት አድርጎ ባትክልቱ ስፍራ ቀበረው፡፡ ይሁን እንጂ ጎረቤቱ ሲቀብረው አይቶት ነበርና ወሰደበት፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ዐይነ-ስውሩ ገንዘቡን ከቀበረበት ለማውጣት ወደ አትክልት ስፍራው ሄዶ ቢፈልገው አጣው፡፡ ጎረቤቱንም ጠረጠረውና በታማኝነት አስመስሎ “ከዚህ በፊት ባትክልቴ ስፍራ ገንዘብ ቀብሬ ነበር፤ አሁንም አንድ ሰው የተበደረኝን ወርቅ መለሰልኝ ስለዚህ የት ባደርገው የሚሻል ይመስልሃል?” ሲል ጠየቀው፡፡ ጎረቤቱም ሁሉንም ለመውሰድ ስለፈለገ “በአንድነት ቅበረው፡፡“ አለው፡፡ ከዛም ጎረቤቱ ለብቻው ሲያስብ ቆየና “በፊት የቀበረውን ገንዘብ ከቦታው ሲያጣው ይህን አሁን ሊቀብረው ያሰበውን ወርቅ አይቀብርም፡፡” ብሎ በማሰብ ሁሉንም በአንዴ ለመውሰድ ሲል የሰረቀውን ገንዘብ ከነከረጢቱ ወስዶ መልሶ እዛው ቦታ ቀበረው፡፡ ዐይነ-ስወሩም በሌሊት መጥቶ የፊተኛውን አውጥቶ በምትኩ አንድ ከረጢት ቀበረና ሄደ፤ ጎረቤቱም ተጠባብቆ ቢያወጣው ጠጠር ሆኖ አገኘው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ሰዋስው

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ስም ወይም ግስ መሆናቸውን በመለየት በየምድባቸው ስር ጻፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| መምህር | መጣ | ቤት | ተማረ |
| ሠራ | ኢትዮጵያ | ተጫወተ | ትምህርት ቤት |
| ተማሪ | ተሳፈረ | ዝንጀሮ | ገነባ |
| ነዳ | አደባባይ | ሄደ | ወቀጠ |
| መጽሐፍ | አነበበ | ህንጻ | መኪና |

| | ስም | ግስ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ቤት | መጣ |
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |
| 9 | | |

ለ. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ባለቤት የሆነውን ቃል ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. እሷ የመምህሯን ምክር ትሰማለች፡፡
የዓረፍተነገሩ ባለቤት = እሷ
ለ. ውሻው ሥጋ በላ፡፡
የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት = ውሻው

1. እሱ ወንበሩን ሰበረው፡፡
2. አፎሚያ ጥርሷን በረሸች፡፡
3. ድመቷ አይጥ ያዘች፡፡
4 . ኃይሉ በሩን ዘጋ፡፡
5. ራህመት ወንድሟን መከረች፡፡

መ. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) የሆነውን ቃል ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. እናቴ ከጎረቤቶቻችን ጋር ቡና ትጠጣለች፡፡
የዓረፍ ተነገሩ ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) = ትጠጣለች
ለ. አካባቢያችን ውብ እና ጽዱ ነው፡፡
የዓረፍተ ነገሩ ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ) = ነው

1. ሰላም በሚኒሚዲያ ክበብ ትሳተፋለች፡፡
2. ናሆም መምህሩን አመሰገነ፡፡
3. ሽማግሌዎች የተጣሉትን አስታረቁ፡፡
4. እታፈራሁ ቁረሷን በላች፡፡
5. አናኗራችን አብሮነትን ያበረታታል፡፡
6. የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡

ሠ. በምሳሌው መሠረት ዓረፍተነገሮቹ ስህተት ካለባቸው በሳጥኑ ውስጥ የ " " ምልክት፤ ትክክል ከሆነ የ " " ምልክት በማድረግ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. አንበሳ የዱር እንስሳ ናቸው፡፡ ×

ለ. የአካባቢያችንን ንጽህና በጋራ እንጠብቅ፡፡ √

1. ዋልያ የኢትዮጵያ ብርቅዬ እንስሳ ነው፡፡ ☐
2. የሸክላ ሥራ የዕደ ጥበብ ማሳያችን ነው፡፡ ☐
3. በመኪና ተሳፍሬ ወደ ጂንካ ሄደ፡፡ ☐
4. ኳስ ሲጫወት እግሩን ተሰበረች፡፡ ☐
5. ደቡብ ክልል የትንሿ ኢትዮጵያ ተምሳሌት ነው፡፡ ☐

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

### ጽሕፈት

ሀ. በምሳሌው መሠረት የባለቤት እና የግስ ስምምነት ስህተቶችን በማስተካከል ዓረፍተ ነገሮቹን በድጋሚ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- እኔና አባቴ አጆራ ፏፏቴን ጎበኘ፡፡

እኔና አባቴ አጆራ ፏፏቴን ጎበኘን፡፡

1. ሀኪሞች ሕሙማንን ትንከባከባለች፡፡
2. በአቅራቢያችን ትምህርትቤቶች ይገኛል፡፡
3. ሁላችንም ቡና ጠጣሁ፡፡
4. በተሰማራበት ሥራ ስኬታማ ሆኑ፡፡
5. ቤቶቹ ተመልሶ ተገነባ፡፡
6. ለጥምቀት ያሆነ ቀሚሶች ይበጣጠስ፡፡
7. እኔ ዳቦ ለመግዛት ሄድን፡፡

8. ኢትዮጵያ 3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አሸንፈዋል።

## መናገር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ተዘጋጅታችሁ ውይይት አድርጉ።

**የመወያያ ርዕስ**

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕስ መሠረት ስለ አገራችን ታዋቂ አትሌቶች በሰበሰባችሁት መረጃ መሠረት ውይይት አድርጉ።

ምሳሌ፡-

ሀ. አትሌት አበበ ቢቂላ
ለ. አትሌት ስለሺ ስህን
ሐ. አትሌት ፋጡማ ሮባ
መ. አትሌት ጌጤ ዋሚ
ሠ. አትሌት ሚሊዮን ወልዴ

# የምዕራፍ ስድስት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የውይይት ምንነትን ከክርክር ጋር በማነጻጸር አብራሩ?

2. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቅጥያዎች በመነጠል ጻፉ?

| | ባለ ቅጥያ ቃላት | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንኪያዎች | | |
| 2 | ወላጆች | | |
| 3 | ሰንሰለታማ | | |
| 4 | ህዝባዊ | | |
| 5 | ጥፋተኛ | | |

3. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቾቻቸውን ጻፉ::

| | ቃላት | ተመሳሳይ ፍች | ተቃራኒ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | በረታ | | |
| 2 | ተሸፈነ | | |
| 3 | ግልጽ | | |
| 4 | ፈጣን | | |
| 5 | ገነባ | | |

4. በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ የተሳሳተውን የባለቤት እና ግስ ስምምነት አስተካክላችሁ ጻፉ::

ሀ. የኢትዮጵያውያን የቀን አቆጣጠር ከሌሎች ተለየች::

ለ. በደቡብ ክልል ውስጥ በርካታ ሰዎች ኖረ::

ሐ. ስፖርት ለጤና ጠቃሚ ናቸው::

# ምዕራፍ 7

# ውሃ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ኢ-መደበኛ በሆነ አደረጃጀት በሚና ጨዋታ ውስጥ ትሳተፋላችሁ፡፡
- አዳምጣችሁ የጽሁፉን ሃሳብ በዝርዝር ትገልጻላችሁ፡፡
- በራሳችሁ አገላለጽ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- መዝሙር አዳምጣችሁ ስለ ውሃ ጥቅም ትጽፋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕስ ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ግስ የተሟላ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

**ውሃ ምንድን ነው?**



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ውሃ ከምን፤ ከምን የሚገኝ ይመስላችኋል?

ለ. ውሃን በቤታችሁ ውስጥ ለምን፤ ለምን ተግባራት እንደምትጠቀሙበት በዝርዝር ተናገሩ?

ሐ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን ጉዳዮች የሚያነሳ ይመስላችኋል?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. “ውሃ ምድን ነው?” በሚለው ምንባብ መሠረት የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የያዙት ሐሳብ ትክክል ከሆነ “እውነት“ ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት“ በማለት በቃል መልሱ፡፡ ለመልሳችሁም ማብራሪያ ስጡ፡፡

1. ውሃ ለሰው ልጅ እንጂ ለእንስሳትና ለእፅዋት አስፈላጊ ነገር አይደለም፡፡
2. ውሃ ለምግብ ማብሰያነት ከማገልገል ባሻገር ለመጓጓዣነት ብቻ ያገለግላል፡፡
3. ንጹህ ውሃ በውስጡ ሌሎች ነገሮችን ማሳየት ይችላል፡፡
4. በውቅያኖስና በባህር ላይ የሚገኘው ውሃ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል፡፡
5. የምንባቡን ሐሳብ በዝርዝር አብራሩ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል አገባባዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ቃል ምረጡ፡፡

1. ወፏ ከዛፎቹ መሃል ካለው ኩሬ ላይ ስትንቦጫረቅ አየሁ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ወንዝ | ሐ. ያቆረ ውሃ |
| ለ. ምንጭ | መ. ባህር |

2. አገራችን በበርካታ ማዕድናት የከበረች ናት።

ሀ. ንጥረ-ነገሮች ሐ. ነዳጅ

ለ. ባህሎች መ. ወርቆች

3. ውሃ መያዣ ያስፈልገዋል።

ሀ. ማፍሰሻ ሐ. ማንጠልጠያ

ለ. ማንቀሳቀሻ መ. ማጠራቀሚያ

4. ውሃ ሕይወት ላላቸው ነገሮች በሙሉ በመሰረታዊነት ያስፈልጋል።

ሀ. በአማራጭነት ሐ. በተጨማሪነት

ለ. በዋናነት መ. በትርፍነት

## ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ይለያያል | ሀ. ማጣት |
| 2. ማግኘት | ለ. ጠጣር |
| 3. ፈሳሽ | ሐ. ይጎዳል |
| 4. መያዝ | መ. ይገናኛል |
| 5. ይጠቅማል | ሠ. መልቀቅ |

## ሐ. በምሳሌው መሠረት ከተሰጣችሁ ቃላት ውስጥ ሌሎች ቃላትን መስርቱ።

| | | |
|---|---|---|
| አለቀሰበት | አለቀ | አለት |
| | ሰቀለ | በሰለ |
| | አለ | ቀለበት |

1.

| | |
|---|---|
| መመጣጠናቸው | |
| | |
| | |

2.

| | |
|---|---|
| ስለመሰከረለት | |
| | |
| | |

3.

| | |
|---|---|
| አመሰቃቀለ | |
| | |
| | |

4.

| | |
|---|---|
| አሰባበረ | |
| | |
| | |

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### መናገር

ሀ. መምህራችሁ "ጤናችን በእጃችን" በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ግጥም በማድመጥ አስመስላችሁ አንብቡ።

ለ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሠረት የግጥሙን መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በአራት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኛቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሐ. በቡድን በመሆን ስለ ውሃ አጠቃቀም የተመለከተ አጭር ጭውውት አዘጋጅታችሁ በድራማ መልክ አቅርቡ፡፡

## ጽሕፈት

ሀ. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ከእነዚህ ተግባራት መካከል በጠዋት ተነስታ አልጋዋን ካነጠፈች በኋላ ፊቷን በውሃ እና በሳሙና ትታጠባለች፡፡
2. ኡፋይሴ ዘወትር ትምህርት ቤት ከመሄዷ በፊት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናለች፡፡
3. ከዛም የደንብ ልብሷን ለብሳ የተዘጋጀላትን ቁርስ ትበላለች፡፡
4. እሷም ወደ ትምህርት ቤት ትገባለች፡፡
5. ቀጥሎም ማታ ላይ ያዘጋጀችውን ደብተሮች በቦርሳ ይዛ እናቷን ተሰናብታ ከአባትዋ ጋር ጉዞ ትጀምራለች፡፡
6. አባቷም ትምህርት ቤቷ በር ላይ እንደደረሱ ስመው ይሸኟታል፡፡

መነሻ

ኡፋይሴ ዘወትር ትምህርት ቤት ከመሄዷ በፊት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናለች፡፡

___

___

___

___

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

## ከሰከላ እስከ ጉባ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የህዳሴው ግድብ እየተገነባ ያለበት ክልል እና ልዩ ቦታ ስም ታውቃላችሁ?

ለ. ስለአባይ ወንዝ የምታውቁትን በዝርዝር ተናገሩ::

ሐ. የአባይ ወንዝ መነሻ ቦታ ማን ይባላል?

የአባይ ወንዝ በአገራችን መልክዓ-ምድር ምዕራብ ጎጃም ዞን ልዩ ስሙ ሰከላ ከሚባል አካባቢ ፈልቆ ጣናን መነሻ አድርጎ ሌሎች ገባር ወንዞችም አብረውት ተቀላቅለው እንዲጓዙ በማድረግ ያለከልካይ ለአያሌ ምዕተ-ዓመታት ለም አፈራችንን እየጠራረገ ለጎረቤት አገራት ሲሳይ በመሆን ለሃገራችን ምንም ጥቅም ሳይሰጥ ቆይቷል።

የአባይን ወንዝ መጠን እየጨመሩና እያበዙ ከሚሄዱ በርካታ ገባር ወንዞች መካከል ወንቃ፣ ጀማ፣ ሙገር፣ ጉደር፣ ደዴሳ፣ ነዲ፣ ዳቡስ፣ ቱሉ፣ አባያ፣

ሙጋ፣ ሱሃ፣ ጉላ፣ ተምጫ፣ ባጫት፣ ጨሞጋ፣ በለሳ፣ ጉማራና ዋቤ ይጠቀሳሉ፡፡ አባይ ዛሬ ላይ ግን እንደ ትናንቱ ሳይሆን ዓይኑን ወደ እናቱ፣ ልቡን ወደ ትውልድ አገሩ፣ እግሩን ወደኋላ ለማዞር የሩጫ መንገዱን ለመግታት ከጉባ ሰማይ ስር አለሁላችሁ ብሏል፡፡ አባይ ከጉባ ሰማይ ስር በጭስ ብዛት የዛሉ ዓይኖች የሚጠብቁት፣ ብርሀን ፈላጊ ዜጎች ተስፋ የሚያደርጉት፣ የአይበገሬነታችን ማሳያ፣ የተፈጥሮ ልግስናችንና የኢትጵያዊነት የክብራችን ግርማ ሞገስ የሆነ ታላቅ ወንዝ ነው፡፡

ሀ. "አባይ ዛሬ ላይ አይኑን ወደ እናቱ አዙሯል፡፡" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. የአባይ ወንዝ መገደቡ ምን ጥቅም ይሰጣል?

በዚህ ታላቅ ወንዝ ላይ ለዘመናት ኢ-ፍትሐዊ ፍርድ ተፈርዶብን የ86 በመቶ የውሃ አመንጭነት ድርሻችን ሳይታይ፤ አይችሉትም ሲሉ ችለን ይህን ታላቁን የህዳሴ ግድብ በመገደብ በኃይል ማመንጫነትና ፈርጀ ብዙ የልማት ጎዳናዎችን የሚያቀናጅ ግዙፍ ተግባር ሆኗል፡፡ ይህ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ካለው ፈርጀ ብዙ ጥቅም በዋናነት የሚጠቀሰው የአገራችንን የኃይል ፍላጎት ከሚሟላት አልፎ ለጎረቤት አገራት ፍትሀዊነት ባለው መልኩ በመሸጥና አብሮ በመልማት በሚደረገው የመደጋገፍ ጉዞ ነው፡፡ በተለይም ለምሥራቅ አፍሪካ የኃይል ትስስር በመፍጠር ያለንን የኢኮኖሚና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ከፍ እንዲል ከማስቻሉም በላይ እንደ አህጉርም ለአፍሪካ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡
ግንባታው እየተካሄደ ያለው በኢትዮጵያ ምድር ከራስ አብራክ በሚፈልቅ ወንዝና በራስ ወጪ በመሆኑ የዘመናት ቁጭታችንን የሚሽር፣ የአብሮነታችንና የመተባበራችን ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ገፀ-በረከት የሆነውን የአባይ ውሃ ጥቅም ላይ ለማዋል ታልሞ በሚሠራው ሥራ የኢትዮጵያዊያን ኩራት በሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኃይል ማመንጫ ላይ ትልቅ ተስፋ ሰንቀንበታል፡፡ ይህ ከድህነት መላቀቂያ የሆነው የሰንደቅ አላማ ፕሮጀክታችን ያለምንም ብድርና እረዳታ በኢትዮጵያዊያን ርብርብ ተገንብቶ በቅርብ ይጠናቀቃል፡፡ በዚህም እኛ የአባይ ዘመን ልጆች ልንኮራ ይገባል፡፡

(ምንጭ፡- አ.አ.ከ አስተዳደር፤ ዝክረ ህዳሴ በአዲስ አበባ፤2013 ዓ.ም፤ ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተጣጥሞ የተወሰደ፡፡)

# ተግባር አንድ:- አንብቦ መረዳት

ሀ. “ከሰከላ እስከ ጉባ” በሚለው ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. የአባይን ወንዝ መጠን እንዲጨምር የሚያደርጉ ገባር ወንዞችን ዘርዝሩ።
2. የህዳሴ ግድብ እየተገነባ ያለው በማን ወጪ ነው?
3. “የአባይ ግድብ የአይበገሬነታችን ማሳያ ነው።” ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ይህን ታሪካዊ ግድብ ለማጠናቀቅ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. የአባይ ወንዝ ግድብ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት በምን መልኩ እንደሚያጠናክር አብራሩ?

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

ሀ. ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ።

1. ተቀላቅለው
2. አያሌ
3. መግታት
4. ዛለ
5. ጥቅም

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቻቸውን ምረጡ።

1. እኛ ኢትዮጵያዊያን ኩሩ ነን።

ሀ. አንገት ደፊ
ሐ. ጉረኛ
ለ. ልበ-ቢስ
መ. ልበ-ሙሉ

2. የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፋይዳ የጎላ ነው።

ሀ. አስፈላጊ　　　　ሐ. ጥናት

ለ. ጥቅም　　　　መ. ጉዳት

3. የኤሌክትሪክ ኃይል ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡

ሀ. በርካታ　　　　ሐ. ጥቂት

ለ. የመብራት　　　　መ. መጠነኛ

4. የአባይን ወንዝ መጠን እየጨመሩ የሚሄዱ በርካታ ገባር ወንዞች አሉ፡፡

ሀ. ጥቂት　　　　ሐ. መጋቢ

ለ. ረጃጅም　　　　መ. በርካታ

5. የምዕተ- ዓመቱ ትልቅ ሥራ በአባይ ወንዝ ላይ እየተሠራ ነው፡፡

ሀ. የመቶ ዓመቱ　　　　ሐ. የሺህ ዓመቱ

ለ. የሃምሳ ዓመቱ　　　　መ. የአስር ዓመቱ

6. ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በቅርቡ ይቋጫል፡፡

ሀ. ይሰፋል　　　　ሐ. ይጠናቀቃል

ለ. ይጀመራል　　　　መ. ይቀጥላል

7. ወንዞቻችን ግርማ ሞገስ ናቸው፡፡

ሀ. ፏፏቴ　　　　ሐ. ማስፈራሪያ

ለ. ኃይል ማመንጫ　　　　መ. ኩራት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ጽሕፈት

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. ትስስር　　　　4. ሲሳይ

2. አብራክ　　　　5. ዘመናት

3. ሰንቀን

## ንግግር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የመከራከሪያ ርዕስ መሠረት አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ እና የክርክር መመሪያን በመከተል ክርክር አከናውኑ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## ሰዋስው

ሀ. በምሳሌው መሠረት ለሚከተሉት ያልተሟሉ ዓረፍተነገሮች ተገቢውን ገላጭ ቃላት በመጠቀም አሟሉ፡፡

1. ሪቻርድ ፓንክረስት ኢትዮጵያዊ ዜግነት አግኝተዋል፡፡
2. እሱ__________ተማሪ ነው፡፡
3. እናቴ __________ የባህል ልብስ ለብሳለች፡፡
4. አዳራሹ__________ስለሆነ ብዙ ሕዝብ ይይዛል፡፡
5. __________ልጅ መጣ፡፡
6. __________አባት አለኝ፡፡
7. __________ህዝብ ተሰበሰበ፡፡
8. __________ውሃ በባልዲ ቀዳሁ፡፡
9. __________ተማሪ የግል ንጽህናውን አይጠብቅም፡፡
10. ቁመቱ__________ስለሆነ መሰላሉ ይሉታል፡፡

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት ገላጭ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም

አሳዩ።

| | |
|---|---|
| 1. ቀይ | 4. ጨካኝ |
| 2. ትልቅ | 5.ሁለት |
| 3. አጭር | 6.ሩህሩህ |

ሐ. ከዚህ በታች በሳጥኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላቶች መካከል ግስ የሆኑትን ብቻ መርጣችሁ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተነሳ | ሰንደቅ-ዓላማ | ጥቁር | አነበበ |
| አንበሳ | አደገ | ቆረጠ | የዋህ |
| ነው | ጠማማ | መምህር | ቀባች |
| ለስላሳ | አሸነፈ | አጸዳ | ኢትዮጵያ |
| ሮጠ | ክብ | አፈር | አበሰ |

ምሳሌ፡- ተነሳ

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ጽሕፈት

ሀ. ከዚህ በታች ያልተጠናቀቁ ዓረፍተ ነገሮችን በተገቢው ግስ አሟልታችሁ ጻፉ።

1. መስከረም ሲጠባ አደይ አበባ_______________።
2. የመጀመሪያዋ ሴት አውሮፕላን አብራሪ ካፒቴን ሙሉእመቤት እምሩ ____________።
3. ኢትዮጵያ የገጠሟትን ጠላቶች ከእግሯ ስር____________።
4. እጃችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ ____________።
5. ትምህርት ለአገር ዕድገት መሠረት ____________።

6. የኮሮና ቫይረስ በሽታን ለመከላከል አካላዊ ርቀታችንን__________::
7. በደቡብ ክልል በርካታ ቋንቋዎች______________::
8. በትምህርት ቤታችን ጠዋት ጠዋት ብሔራዊ መዝሙር________::

ለ. ከታች በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ አምስት ግሶችን ካወጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር ስሩባቸው::

አንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ:: ባልየው ቀኑን ሙሉ ከሐይቅ ውስጥ ዓሣ ያጠምዳል:: ሚስትየው ዓሳዎቹን ትሸጣለች:: ሆኖም የዓሣ ገበያ ብዙም አስደሳች አይደለም:: ስለዚህ ገቢያቸው አነስተኛ ነበር:: ቢሆንም ግን ሁልጊዜ የበለጠ ይጥራሉ::

## ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ::

## አህያ እና በሬ

አንድ ገበሬ ሁለት በሬዎች እና አንድ አህያ ነበሩት:: አንደኛው በሬ በጣም ከስቶ ነበር:: አህያው ደግሞ በጣም ወፍሮ ነበር:: አህያው አንድ ቀን በሬውን “ምነው ሰውነትህ ከሳ?” ሲል ይጠይቀዋል:: በሬውም “እርሻ ስለበዛብኝ፣ እረፍትና በቂ ሣር ስላጣሁኝ ነው::” አለው:: አህያውም ያዝንና “አሞኛል ብለህ ተኛና ትንሽ ቀን እረፍ::” አለው:: በሬውም አህያውን “አሁን ገና ጥሩ ምክር መከርከኝ::” አለና፣ ወዲያውኑ እያነከሰ ወደቤቱ ሄደ::
ባለቤቱም በእርሻ ወቅት በሬው በማንከሱ በጣም አዘነ:: ቶሎ እንዲድንለት ሣር እና ውሃ ይሰጠው ጀመር:: ከእርሻውም እንዲያርፍ አደረገው:: እስከዚያው ድረስ ግን አህያውን ከሌላኛው በሬ ጋር ጠምዶ እርሻውን ያርስ ጀመር:: አህያው ግን እንደ በሬው ሊያርስለት አልቻለም:: ስለዚህ ይናደድና ጀርባው እስኪመለጥ ድረስ በጅራፍ ሲገርፈው ይውላል::

እረፍት ሲያደርግ፣ ሲበላና ሲተኛ የዋለው በሬ አህያው ከእርሻ ሲመለስ ያገኘዋል፡፡ “አህያ፤ እንዴት ዋልክ?” አለው፡፡ አህያውም “እኔስ ደህና ውያለሁ፤ ለመሆኑ አንተ እንዴት ዋልክ?” ሲል መልሶ ይጠይቀዋል፡፡ በሬውም “የኔን ነገር ተወው ባክህ እጅግ በጣም አሞኝ ዋለ፡፡” አለው፡፡ ከዚያም በሁኔታው የተናደደው አህያ፣ “አይ!. . .መታመምህስ ባልከፋ” ይለዋል፡፡ “እንዴት?” ሲል በሬው አህያን በድንጋጤ ይጠይቃል፡፡ “እንዲያው አንድ አስደንጋጭ ነገር ሰምቼ በጣም አዘንኩ፡፡” አለው፡፡ አያ በሬም “ምን ሰማህ?” ይላል፡፡ “ይኸ በሬ ቶሎ የማይድን ከሆነ፤ ሰውነቱ ይበልጥ ከመክሳቱ በፊት አርደን ሥጋውን እንካፈለው እያሉ ሲማከሩ ሰማሁ፡፡”አለው፡፡ በሬውም በሰማው ነገር ይደናገጥና ማንከሱን አቁሞ፣ እያገሳና እየፈነጠዘ ወደቤቱ ሄደ፤ ይባላል፡፡

(ምንጭ፡- ባዬ ይማም፣ 2002፣አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፣ከገፅ 101-102 ለንባብ ማስተማሪያነት ተሸስሎ የቀረበ)

## የምዕራፍ ሰባት የክለሳ ጥያቄዎች

1. አምስት የተለያዩ ገላጭ ቃላትን በዓረፍተነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ።

2. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ጻፉ።

ሀ. ዛለ　　ሐ. የራስ አብራክ　　ሠ. ደባ

ለ. ለገሰ　　መ. ህቡዕ　　ረ. ነፈገ

3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. ዕድገት　　ሐ. ታላቅ　　ሠ. ክብር

ሀ. የግል　　መ. ፈሪ　　ረ. መሸጥ

4. ከሚከተሉት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ግሶችን ብቻ በመምረጥ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሙልሙል | ደማቅ | ተሳተፈ | ጠመኔ | መርካቶ |
| ቻለ | ወረቀት | አስተዋይ | አከናወነ | ስስ |
| ውሃ | አደገ | ከተማ | ጸጉራም | አዳበረ |

# ምዕራፍ 8

# መደራደር

**የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፦

- አዳምጣችሁ ተራ በተራ በንግግር ትሳተፋላችሁ፡፡
- በግላችሁ አንበባችሁ ዝርዝሩን ታብራራላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን ህግና ደንብ ትጽፋላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ ትነጥላላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

**ትሁቷ ፋሲሌ**





## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ የምንባቡ ርዕስ ስለምን የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ለ. ሰዎች ሲደራደሩ አይታችሁ ታውቃላችሁ?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በቃል ስጡ፡፡

1. ፋሲሌ ሊቀ-ትሁት የሚል ቅፅል ስም የተሰጣት በምን ምክንያት ነው?
2. ፋሲሌ በምታገኝው አጋጣሚ ሁሉ የምታስተምረው ስለምን ጉዳይ ነው?
3. ሁለት ተማሪዎች ለድብድብ ሲጋበዙ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ከድርድሩ በመነሳት ከሁለቱ ጓደኛሞች ጥፋተኛው ማነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ምክንያታችሁን ተናገሩ?
5. ከምንባቡ ምን መልዕክት አገኛችሁ?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ፍርድ | ሀ. አላስፈላጊ |
| 2. ትሁት | ለ. ሰበብ |
| 3. አልባሌ | ሐ. አየች |
| 4. ተመለከተች | መ. ቅን |
| 5. ምክንያት | ሠ. ብይን |

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ።

1. ልዩነት
2. መፍታት
3. ጻብ
4. ሩቅ
5. መውሰድ
6 . መነሻ
7. ማጠናቀቅ

ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተመሳሳይ ፍቻቸውን ምረጡ።

1. መሰሪ

ሀ. ተንኮለኛ ለ. ወረኛ ሐ. ወረተኛ መ. ሠራተኛ

2. ልፍስፍስ

ሀ. ጠንካራ ለ. የሚለፋ ሐ. አቅመቢስ መ. ብርቱ

3. ዘለፋ

ሀ. ምርቃት ለ. ስድብ ሐ. ዘፈን መ. ስልጣን

4. ተለጠጠ

ሀ. ተዘረጋ ለ. ተጣጠፈ ሐ. ታጠፈ መ. ተዘነጋ

5. ማዋሃድ

ሀ. ማደባለቅ ለ. አንድ ማድረግ ሐ. መቀላቀል መ. ሁሉም

መ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማጥበቅ እና በማላላት ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም የሚሰጡ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ:- እንጨቱን ጥፍር አድርጎ አሰረው።

ጥፍር = ሲጠብቅ = ጥብቅ ማድረግ

ሲላላ = የአካል ክፍል

1. ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዱ በፊት ቁርሱን በላ።

2. ነስረዲን ከተቀመጠበት ቀና ብሎ መጻፍ ጀመረ፡፡
3. የአማርኛ መጽሀፍ አለኝ፡፡
4. መብራቱ በራ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### ጽሕፈት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

1. አመራች
2. መገልገል
3. ይማሩበታል
4. ባለጋራ
5. ወዳጅ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### መናገር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕስ ላይ ዝግጅት በማድረግ እና የንግግር ሕጎችን በመከተል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ንባብ

## ድርድር



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ድርድር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ሱቅ ተልካችሁ እቃ ተደራድራችሁ ገዝታችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት እንደነበር ተናገሩ፡፡

ሐ. ምንባቡ ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

ወይዘሮ የኔነሽ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ልጅ አለቻቸው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ለትምህርቷ የሚሆን አጋዥ መፅሐፍ ሊገዙላት በአካባቢያቸው ወደሚገኝ የመፅሐፍት መደብር አቀኑ፡፡ ከ15 ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ ከአንድ የመፅሐፍት መደብር ውስጥ ገብተው መጣራት ጀመሩ፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ፡- እዚህ ሱቅ! ኧረ እዚህ ሱቅ !

ባለመደብር፡- አቤት ! ምን ልርዳዎት?

ወ/ሮ የኔነሽ፡- ለ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጋዥ መፅሐፍ ፈልጌ ነበር፡፡

ባለመደብር፡- “የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጋዥ መፅሐፍ” የሚል አለ፡፡ ይኸው፡፡

ወ/ሮ የኔነሽ:- ዋጋው ስንት ነው?

ባለመደብር:- ዋጋው 80 ብር ብቻ።

ወ/ሮ የኔነሽ:- እያገላበጡ እያዩት እንዴ! ቀንስልኝ እንጂ 80 ብር! ዋጋው በጣም ውድ ነው።

ሀ. ወይዘሮ የኔነሽ መጽሀፍ የሚገዙት ለማን ነው?

ለ. ከዚህ በኋላ ምን የሚገጥማቸው ይመስላችኋል?

ባለመደብር:-በቃ ሰባ አምስት ብር ውሰዱት አዲስ መጽሀፍ ነው። በዛ ላይ መጽሀፉን ሳመጣ የትራንስፖርት፣ የተሸካሚ ብቻ ብዙ ወጪ አውጥቼበታለሁ።

ወ/ሮ የኔነሽ:-ኧረ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ መጨመር ጥሩ አይደለም። በጅምላ ስታመጡ ቅናሽ እንዳለው እናውቃለን።

ባለመደብር:- እሺ በስንት ብር ይገዙኛል?

ወ/ሮ የኔነሽ:- እኔ የምገዛው መጽሐፉ ላይ በተቀመጠው የዋጋ መጠን ነው። ስልሳ ብር።

ባለመደብር :-ኧረ ብዙ ወጪ አውጥቻለሁ ባይሆን ሰባ ብር ላድርግሎት።

ወ/ሮ የኔነሽ:- ስልሳ ብር ከሸጥክ ሽጥልኝ፤ የማትሸጥልኝ ከሆነ ይቅርብኝ። ከሸጥክ ይኸው ብሩን ያዝ።

ባለመደብር:- እሺ! ባይሆን ለሌላ ጊዜ ደንበኛ እንሆናለን።

ወ/ሮ የኔነሽ:-- እሺ አመሰግናለሁ! ብለው መጽሀፉን ገዝተው ወደቤታቸው ተመለሱ። ወደቤታቸ ሲደርሱ ለልጃቸው መጽሀፉን ሰጧት፤ ልጃቸውም በእናቷ ድጋፍ እጅግ ተደስታ እናቷን አመሰግና፤ መጽሀፉን ማንበብ ጀመረች።

# ተግባር አንድ:- አንብቦ መረዳት

## ሀ. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ባለመደብሩ ምን ልርዳዎት ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ወ/ሮ የኔነሽ ወደመደብሩ የሄዱት ምን ለማድረግ ነው?
3. ባለመደብሩ መጽሐፉን ከ60 ብር በታች ወይስ በላይ ነው ያመጣው? መልሳችሁን በምክንያት አስረዱ።

4. ወ/ሮ የኔነሽ መጽሐፉን ከ60 ብር በላይ አልገዛውም ብለው በአቋሟቸው እንዲጸኑ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድን ነው?

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### ቃላት

**ሀ. በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃለት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አጋዥ | ሀ. መሄድ/ማስተካከል |
| 2. ያልተገባ | ለ. ማገዝ |
| 3. መርዳት | ሐ. ውድቀት |
| 4. ኪሳራ | መ. ረዳት/ደጋፊ |
| 5. ማቅናት | ሠ. አላስፈላጊ |

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡**

1. ወጪ
2. ውድ
3. መሸጥ
4. መስጠት
5. ጫኝ

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡**

1. ደንበኛ
2. ኪራይ
3. ሱቅ
4. ሸጠ
5. ከፈለ
6. ጨመረ

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## ሰዋስው

### ሀ. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መጨረሻ ላይ በቅንፍ ውስጥ ከተቀመጡት ቃላት መካከል በመምረጥ የዓረፍተነገሩን ሐሳብ አሟሉ፡፡

1. የባቡር__________እየተሠራ ነው፡፡ (መንገድ/መንገዶች)
2. ከኢትዮጵያ ወደ ጎረቤት አገሮች የማይፈስ________________አዋሽ ነው፡፡ (ወንዝ/ወንዞች)
3. በግቢያችን ውስጥ በርካታ የጓሮ ___________ተክለናል፡፡ (አትክልት/አትክልቶች)
4. መኪና፣ ባቡር እና አውሮፕላን ዘመናዊ ____________ናቸው፡፡ (መጓጓዣ/መጓጓዣዎች)
5. በበዓል ቀን የተለያዩ የባህል________________ይለበሳሉ፡፡ (ልብስ/ልብሶች)

### ለ. በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የሚከተሉትን አገላለጾች አሟሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| አምቡላ | ላጨ | ተደፋ | ይጣላል |
| ይራመዳል | ገጠመ | አብራሪ | አወጣች |

1. እንጀራ ተጋገረ ካልን ድፎ ዳቦ___________እንላለን፡፡
2. እባብ በልቡ ይሳባል ካልን ሰው በእግሩ_________________እንላለን፡፡
3. ጠላ ይጠመቃል ካልን ጠጅ_____________እንላለን፡፡
4. ለቡና እና ለጠላ አተላ ካልን ለጠጅ __________እንላለን፡፡
5. ጠላ ጠመቀች ካልን አረቄ______________እንላለን፡፡

6. ለጽሑፍ ጻፊ ካልን ለግጥም__________እንላለን፡፡

7. መኪና አሽከርካሪ ካልን አውሮፕላን__________እንላለን፡፡

8. ለበግ ጸጉር ሽለተ ካልን ለሰው ጸጉር__________እንላለን፡፡

ሐ. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቃሉንና ቅጥያውን ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ:- ኢትዮጵያዊ = ኢትዮጵያ- ኣዊ

1. ቦርሳዎች
2. በጎች
3. ልባችን
4. ወንድማችን
5. ምርታማ

መ. ከሚከተለው ሳጥን ውስጥ የመነሻ እና የመድረሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃላትን በየምድባቸው አስቀምጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መጣችሁ | እንደተጻጻተ | ደረጃዎች |
| ከህዝብ | ተኛች | የተማሪ |
| አስመከረ | ታሪካዊ | ወጥመዶች |
| ልባም | በቴሌቪዥን | ስለአሁን |

የመነሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃላት

1. ከህዝብ
2.
3.
4.
5.
6.


የመድረሻ ቅጥያዎችን የያዙ ቃላት

1. መጣችሁ
2.
3.
4.
5.
6.

ሠ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቅጥያዎችን በመጠቀም ባለቅጥያ ቃላትን መስርቱ፡፡


ምሳሌ፡- - ኦች = እርሳሶች

ኣማ = አፈራማ




ረ. የሚከተለውን የቀለም እና የቁጥር ቅደም ተከተል በመከተል የቤተሰብ አቆጣጠርን ተራበተራ በቅደም ተከተልን ጻፉ፡፡

መነሻ




| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንተቤ | ፍናጅ | ምንቹላት | እስልጥ | ቅም አያት |
| ቅናጅ | አመልጥ | ድርባቴ | ልጅ | ቅድመ አያት (ቅድም አያት) |
| ቅማንት | አያት | አንጅላት | ሽማንት | አባት/ እናት |

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ጽሕፈት

ሀ. በምሳሌው መሠረት ስም፣ ገላጭ እና ግስን በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ።






ምሳሌ፡- አረንጓዴ ሹራብ ተገዛልኝ።

1.

2.

3.



# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## ንግግር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሠረት ስለ ትምህርት ቤታችሁ የተማሪዎች ሕግና ደንብ መረጃ በመሰብሰብ እና ዝግጅት በማድረግ የንግግር መመሪያን ተከትላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡ ፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡

### ሞኟ አህያ

በድሮ ጊዜ ክፉ ቀን መጣና ፍጥረታት ሁሉ የሚልሱት የሚቀምሱት አጡ፡፡ ክፉ ቀኑ የመጣበት ምክንያትም ባለመታወቁ ሁሉም በየፊናው ለማወቅ ይጥር ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብ እና አህያ ክፉ ቀን የመጣበትን ምክንያት ለማወቅ ይወያዩ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ከመካከላቸው አንዱ ኃጢአት በመሥራት ይሆናል ብለው ስለገመቱ እያንዳንዳቸው የሰሩትን ኃጢአት ሊናዘዙ ተስማሙ፡፡ ኃጢአት ሰርቶ የተገኘም ሊፈረድበት ነበር፡፡

በመጀመሪያ አቶ አንበሳ ተናገረ፡- “አንድ ቀን አንዲት ላም ከበረት ሰብራ ወጥታ ስላገኘኋት በልቻታለሁ፡፡ ይህ ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ፡፡” አለ፡፡ እነሱም አንበሳን ሲመለከቱት ግርማው እጅግ የሚያስፈራ ስለነበር “በረት ውስጥ መተኛት ሲገባት በረት ሰብራ መውጣቷ የራሷ ጥፋት እንጂ የርስዎ አይደለም፡፡” አሉት፡፡ ነብር ደግሞ በፋንታው ተነስቶ “አንድ ቀን ምግብ ፍለጋ ጫካ ስዘዋወር አንድ የፍየል ጠቦት ከእረኞች አምልጦ ጫካ ውስጥ ቅጠል ሲቀነጥስ አግኝቼ እሱን በልቻለሁ፡፡ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ፡፡” አለ፡፡ እነአንበሳም “ጥፋተኛው ከእረኞች አምልጦ ጫካ የገባው ፍየል እንጂ አንተ አይደለህም፡፡” አሉት፡፡

ጅብ ደግሞ ኃጢአቱን እንዲህ ሲል ተናዘዘ፡፡ “አንድ ቀን ሌሊት ምግቤን ፍለጋ መንደር ለመንደር ስዘዋወር አንዲት በግ እቤት ውስጥ ከማደሪያዋ ሆና ነገር ግን ላቷን በቀዳዳ ወደ ውጭ አስወጥታ አግኝቼ ቆርጬ በልቻለሁ፡፡ ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ፡፡” አለ፡፡ የተቀሩት እንስሳትም “ጥፋቱ ላቷን ከውጭ ያሳደረችው በግ እንጂ ያንተ ስላልሆነ ልንፈርድብህ አንችልም፡፡” አሉት፡፡

በመጨረሻም አህያ ኃጢአቷን ለመናገር ተነሳችና፤ “አንድ ቀን ጌታዬ አንድ ጆንያ ሙሉ እህል አሸክሞኝ ወደ ገበያ ስሄድ በመንገድ ላይ ዘመድ አጋጠመውና ቆሞ ሲያወራ ወደ መንገዱ ዳር ሄጄ ሣር ነጭቼ በልቻለሁ፡፡ ይህ ኃጢአት ከሆነ ፍረዱብኝ፡፡” አለች፡፡ እነአንበሳም አህያን “በእኛና በወገኖቻችን ላይ ይህን ሁሉ መአት ያመጣሽ አንቺ ነሽ፡፡ ምክንያቱም ጌታሽ ከዘመዱ ጋር ሲያወራ ቆመሽ መጠበቅ ሲገባሽ ሣር መንጨትሽ ከፍተኛ ኃጢአት ነው፡፡” ብለው ተከፋፍለው በሏት ይባላል፡፡

(ምንጭ፡- ፈቃደ አዘዘ፣ የስነ-ቃል መምሪያ፣ 1991ዓ.ም፣ ገጽ78
ለንባብ ትምህርት ማስተማሪያነት ተጣጥሞ የተወሰደ)

# የምዕራፍ ስምንት የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሚከተሉትን ስሞች፣ ገላጮች እና ግሶችን በማጣመር ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ረጅም | ከተማ | ቀይ | ጀግና |
| እናት | ነው | አለችኝ | ቀሚስ |
| ውብ | አየሁ | ፎቅ | ለብሳለች |

2. ከአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ጋር በመሆን ስለትምህርት ቤታችሁ የተማሪዎች ሕግና ደንብ በተመለከተ በክፍላችሁ ውስጥ ንግግር በማድረግ በተወያያችሁት መሰረት በክፍል ውስጥ መከበር ያለባቸውን ሕጎች በሚገባ በመጻፍ በክፍል ውስጥ ለሁሉም ተማሪ በሚታይ ቦታ እንዲለጠፍ አድርጉ፡፡

3. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ስለትምህርትቤታችሁ የተማሪዎች ህግ እና ደንብ በሰንደቅ ዓላማ መርሀ-ግብር ላይ ንግግር አቅርቡ፡፡

4. የሚከተሉት ቅጥያዎች የመነሻ ወይም የመድረሻ ቅጥያዎች መሆናቸውን በመለየት ከቃላት ጋር በማጣመር ጻፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| - ኣቸው | እንደ- | -ኣዊ | - ኦች |

# ምዕራፍ 9

# መገናኛ ብዙኃን

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- መቅረጸ ድምጽ ያዳመጣችሁትን ዋና ሃሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- አንብባችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፡
- ነጠላ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ጥገኛ መስተጻምርን ተጠቅማችሁ ዐረፍ ተነገር ታዋቅራላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

## የሚኒ ሚዲያዋ ፍሬ



## ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. በትምህርትቤታችሁ ምን ምን ክበባት አሉ? ዘርዝሯቸው፡፡

ለ. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ምን ሊነገራችሁ ይችላል?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በቃል አብራሩ፡፡

1. ኤደን በሥራዋ ምን አይነት ሠራተኛ ናት?
2. በክበባት መሳተፍ የጀመረችው የስንተኛ ክፍል ተማሪ እያለች ነበር?
3. ኤደን ዜና ለማቅረብ ወደ መድረክ ስትወጣ ተማሪዎች የሚያጨበጭቡላት ለምን ይመስላችኋል?
4. በትምህርት ቤታችሁ የሚኒ-ሚድያ ክበብ ምን ዓይንት ሥራ ይሠራል? እናንተስ ትሳተፋላችሁ?
5. የሚኒ-ሚድያ ክበብ ተሳትፎዋ አሁን ለደረሰችበት ስኬት ምን አስተዋጽኦ አድርጎላታል ትላላችሁ?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሽልማት | ሀ. ከበሬታ |
| 2. ግንባር ቀደም | ለ. ማበረታቻ |
| 3. አንቱታ | ሐ. ታታሪ |
| 4. ስኬታማ | መ. ፊት መሪ |
| 5. ዘመን | ሠ. ጊዜ |
| | ረ. ውጤታማ |

ለ. በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መሸ | ሀ. ሁካታ |
| 2. አበቃ | ለ. ሰጠ |
| 3. ፀጥታ | ሐ. ነጋ |
| 4. ተቀበለ | መ. ከለከለ |
| 5. አበረከተ | ሠ. ጀመረ |

ሐ. የሚከተሉትን አገላለጾች (አባባሎች) በተሰጡት ቃላት አሟሉ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጸጉር | ጠላ | ጥርስ | ውሃ | አፍንጫ | ቡና | ዓይን |

1. የፈረስ ጭራ የመሰለ ቡና
2. በረዶ የመሰለ______________
3. ስንደዶ የመሰለ______________
4. የዶሮ ዓይን የመሰለ______________
5. የባቄላ አበባ የመሰለ______________
6. ጥቁር ሀር የመሰለ______________
7. ኩል የመሰለ______________

# ወደረኛ እና ጥገኛ መስተፃምር

መ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ወደረኛ እና ጥገኛ መስተፃምሮች ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሀ. ሬድዮ እና ቴሌቪዥን የመገናኛ ብዙሃን አይነቶች ናቸው። = እና

ለ. በባቡር መሄድ ደስ ይለኛል። =በ

1. ፋጡማ ከትምህርት ቤት መጣች።
2. ትምህርቴን ስጨርስ በመምህርነት ሙያ እሰማራለሁ።
3. ወተት በዳቦ እወዳለሁ።
4. ጎበዝ እና ጨዋ ተማሪ መሆን ይኖርብናል።
5. በስፖርት ውድድር ትምህርት ቤታችን አሸናፊ ሆነ።
6. ለጓደኛዬ ጥሩ መሆን አለብኝ።
7. እርሳስ ወይም እስክሪብቶ አውሰኝ።

| ጥገኛ መስተጻምሮች | ወደረኛ መስተፃምር |
|---|---|
| በግስ ወይም በስም ላይ በመጨመር አንድ ዐረፍተ ነገር ሙሉ መልእክት እንዲያስተላልፍ የማስማማት ሚና ያላቸው መስተጻምሮች ጥገኛ መስተጻምሮች ይባላሉ። | ተመሳሳይና ተመጣጣኝ የሆኑ ነገሮችን ወይም ድርጊቶችን የሚያጣምሩ መስተፃምሮች ወደረኛ መስተፃምሮች ይባላሉ። |
| ምሳሌ፡- ሀ. ስለመጣ<br>ለ. በመኪና<br>ሐ. ከወሰደብኝ | ምሳሌ፡- ሀ. ሴትና ወንድ<br>ለ. አባትና እናት<br>ሐ. አጭርና ረዥም<br>መ. አባት ወይም እናት |

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### ጽሕፈት

ሀ. የሚከተሉትን ወደረኛ መስተፃምሮች በመጠቀም በእያንዳንዳቸው ሦስት፣ ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

እና ወይም

መ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለይታችሁ አውጡ።

ምሳሌ፡- አባቴ ነጋዴ ነው፤ ይሁን እንጅ ስኬታማ አይደለም። = ይሁን እንጂ

1.ዛሬ ደብተራችን ይታረማል፤ምክንያቱም ትናንት የቤትሥራ ተሰጥቶናልና።

2.ጋዜጠኛው በጣም ጎበዝ ነው፤ በመሆኑም ሽልማት ይገባዋል።

3.ቃሪያ መመገብ እወዳለሁ ነገር ግን ያቃጥለኛል።

4.ማንበብ ያስደስተኛል እንጂ ዝምብዬ ጊዜዬን ማባከን አልወድም።

5.መምህራችን ጨዋ ተማሪዎችን ያበረታታሉ፤ ስለዚህ ሁላችንም ጨዋዎች መሆን አለብን።

## ክፍለ ትምህርት አራት

### ንባብ

## የሚዲያ ፊርጦች

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የምንባቡ ርዕስ ስለምን የሚነግራችሁ ይመስላችኋል?

ለ. መገናኛ ብዙኀን ማለት ምን ማለት ነው? የምታውቁትን ተናገሩ።

## መዓዛ ብሩ

ጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ የወጣቶች ተምሳሌት፣ የሴቶች አርአያ፣ የብርታት ማሳያ፣ የሬዲዮ ፈርጥ፣ የጋዜጠኝነት ምልክት ናት በማለት አድናቂዎቿ እና የሙያ አጋሮቿ ይመሰክራሉ፡፡ መዓዛ የዛሬ 20 ዓመት ገደማ የመጀመሪያው ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ሲመሠረት የቅዳሜ ከሰዓት በኋላ የጨዋታ ፕሮግራም በዚሁ ጣቢያ ማቅረቧን ተያያዘቻው፡፡ ይህን አቅም በመጠቀም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ማገባደጃ ሰሞን በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የግል ይዞታ የሆነውን ሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ሬድዮ ጣቢያን መሰረተች፡፡ ሬዲዮው በኢትዮጵያ ተወዳጅ እንደሆነ እንዲቀጥል ከፍተኛ ጥረት አደረገች፡፡ በዚህ ምክንያት የዓለም ሬዲዮ ቀን በሚከበርበት በ2012 ዓ.ም በሬድዮ ዘርፍ የሕይወት ዘመን ምርጥ ጋዜጠኛ ሆና ተሸለመች፡፡

ሀ. ጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ በመጀመሪው ኤፍ.ኤም 97. 1 የጀመረችው ፕሮግራም ምን የሚል ነበር?

ለ. ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን የጋዜጠኝነት ሙያውን የተቀላቀለወ በስንት ዓ.ም ነው?

## ደጀኔ ጥላሁን



ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን የተወለደው በ1948 ዓ. ም በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ አዲሱ ገበያ በሚባል አካባቢ ነው፡፡ የጋዜጠኝነቱን ዓለም ከመቀላቀሉ በፊት በመምህርነት ሙያ ያገለገለው ደጀኔ፤ ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ስሙን በጋዜጠኝነት ዓለም የተከለ ባለሙያ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሬድዮ ብሔራዊ አገልግሎት በቆየባቸው 26ዓመታ የጋዜጠኝነት ህይወቱ፤ በተለይም “ከመጽሀፍት ዓለም” በተሰኘ ፕሮግራም ላይ በማራኪ ድምጹ በተረካቸው አያሌ መጻሕፍት ብዙዎች ያስታውሱታል፡፡ ከተለያዩ የጥበብ ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ በርካታ የኪነ-ጥበብ ሥራዎችንም ሰርቷል፡፡ “የኪነ-ጥበባት ምሽት”ና “የእሁድ ጧት ፕሮግራም” ማዘጋጀት እና ማቅረብ ሌላኛው የሚታወቅበት ሥራው ነበር፡፡ አንጋፋው ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን ከመስከረም 2004 ዓ.ም ጀምሮ

"ደጀኔ ጥላሁን ፕሮሞሽን" በሚል ድራማ፣ ማስታወቂያ እና ዶክመንተሪ ፊልሞችን በመሥራትና በሌሎች መሰል ተግባራት ላይ መሰማራቱ ይታወቃል፡፡

## ፀሐይ ተፈረደኝ

በኢትዮጵያ ሬድዮ ሲቀርቡ በነበሩት "በሕይወት ዙሪያ"፣"የሴቶች መድረክ"፣ "የእሁድ ጠዋት ፕሮግራም" ላይ ድምጿን ደጋግመን ስንሰማው ኖረናል፡፡ የኢትዮጵያ ሬድዮ ፕሮግራም በሆነው ተወዳጁ "ኢትዮጵያን እንቃኛት" የሬድዮ ፕሮግራም ሲነሳ አብረው ከሚታወሱ ድምጾች አንዱ የእሷ ድምጽ ነው፡፡



በረጅም የጋዜጠኝነት ሥራ ዘመኗ ብዙዎች የሚያስታውሷት በየሳምንቱ እሁድ ረፋድ ላይ ይደመጥ በነበረው የጦር ኃይሎች የሬድዮ ፕሮግራም ላይ ነው፡፡ ፀሐይ እንደጋዜጠኛ ማራኪ ፕሮግራም ቀማሪ፤ እንደ ሴት ደግሞ ፅናት አስተማሪ ናት፡፡ በ2012 ዓ.ም የዓለም ሬዲዮ ቀን ሲከበር ጋዜጠኛ ፀሐይ ተፈረደኝ በሬድዮ ጋዜጠኝነት ላደረገችው ከፍ ያለ አስተዋፅዖ የሕይወት ዘመን ምርጥ ጋዜጠኛ ተሸላሚ እንድትሆን ተመርጣለች፡፡

## ደምሴ ዳምጤ



የኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኞች ታሪክ ሲጠቀስ ከማይዘነጉት አንዱ ደምሴ ዳምጤ ነው፡፡ ደምሴ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደረበትን የስፖርት ፍቅር በማጎልበት በ1968ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በኢትዮጵያ ሬድዮ በቋሚነት መሥራት ጀመረ፡፡ ደምሴን አንስቶ 1980 ዓ.ም የምሥራቅና የመካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ በተለይም የኢትዮጵያና የዝምባቡዌ የፍፃሜ ጨዋታ አለማንሳት አይቻልም፡፡ የዋንጫ ጨዋታው የተጠናቀቀው በመለያ ምት ነበር፡፡ ይህን ታሪካዊ ጨዋታ ያስተላለፈበት መንገድ ከማንም አዕምሮ አይጠፋም፡፡ ሌላው ደምሴ በሥራ በቆየባቸው ከ30 አመታት በላይ ከሚታወሱት ሥራዎቹ ውስጥ በባርሴሎና ኦሎምፒክ ደራርቱ ቱሉ

የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ስታሸንፍ ውድድሩን በቢ.ቢ.ሲ ሬዲዮ ሌሊቱን ሙሉ ተከታትሎ በማለዳው ለኢትዮጵያ ህዝብ በአስደናቂ አቀራረብ የምሥራቹን አበሰረ። ይህን ታላቅ የስፖርት ሰው በሕይወት ካጣነው ጥቅምት 26/2013ዓ.ም ስምንተኛ አመቱን ይዟል፡

## እሌኒ መኩሪያ



በ1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሥራውን በይፋ ሲጀም በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ የታየችው ሴት ጋዜጠኛ እሌኒ መኩሪያ ነበረች። ጋዜጠኛ እሌኒ በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ታሪክ ውስጥ ደማቅ አሻራ አላት።
በእንግሊዝኛ ቋንቋ የጋዜጠኝነት ሙያ ከኢትዮጵያ እስከ እንግሊዙ ቢ.ቢ.ሲ ሬድዮ በወርቃማ ድምጿ አገልግላለች። ቢ.ቢ.ሲ ላይ አፍሪካዊቷ ኮከብ የተባለች ጋዜጠኛ ነበረች።

(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሬዲዮ 80ኛ ዓመት የተዘጋጀ ልዩ መጽሔት፤ 2013 ዓ.ም)

# ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. ጋዜጠኛ ደጀኔ ጥላሁን በማራኪ ድምፁ መጽሀፍትን በመተረክ የሚታወቅበት ፕሮግራም ምን ይባላል?

   ሀ. ኢትዮጵያን እንቃኛት  ሐ. የኪነ-ጥበባት ምሽት

   ለ. ከመጻሕፍት ዓለም  መ. ጨዋታ

2. የ1980 ዓ.ም የኢትዮጵያና የዝምባቡዌ የምሥራቅና የመካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ የዘገበው ጋዜጠኛ ________ ይባላል።

   ሀ. መዓዛ ብሩ  ሐ. ደጀኔ ጥላሁን

   ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ  መ. ደምሴ ዳምጤ

3. "ኢትዮጵያን እንቃኛት" የሬድዮ ፕሮግራም ሲነሳ አብረው ከሚታወሱት ድምጾች አንዱ የጋዜጠኛ ድምጽ ነው።

ሀ. መዓዛ ብሩ  ሐ. እሌኒ መኩሪያ

ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ  መ. ደጀኔ ጥላሁን

4. ለመጀመሪ ጊዜ በቴሌቪዥን መስኮት ለህዝብ የታየች ሴት ጋዜጠኛ ናት?

ሀ. መዓዛ ብሩ  ሐ. እሌኒ መኩሪያ

ለ. ፀሐይ ተፈረደኝ  መ. "ሀ" እነ "ለ" መልስ ናቸው

5. ጋዜጠኛ____________የመጀመሪያ የግል ይዞታ የሆነውን ሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ሬድዮ ጣቢያን መሰረተች፤

ሀ. ፀሐይ ተፈረደኝ  ሐ. ማህደር ሰሎሞን

ለ. እሌኒ መኩሪያ  መ. መዓዛ ብሩ

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### መናገር

መምህራችሁ በሚያስደምጧችሁ መረጃ መሠረት የመረጃውን ዋና ሐሳብ በመለየት ንግግር አድርጉ።

## ክ
## ፍለ ትምህርት ስድስት

### ቃላት

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ።

1. ፅናት
2 አስተዋጽኦ
3 አጋር
4. ማገባደጃ
5. መዘንጋት
6. ማጎልበት

ለ. ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ደማቅ | ሀ. ነቀለ |
| 2. መጨረሻ | ለ. አስቀያሚ |
| 3. ተከለ | ሐ. ደብዛዛ |
| 4. ማራኪ | መ. መዘንጋት |
| 5. ማስታወስ | ሠ. መጀመሪያ |

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

## ጽሕፈት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. ፕሮግራም
2. አበሰረ
3. አሻራ
4. ኮከብ
5. ማስተዋል
6. መምህር

ለ. በምሳሌው መሠረት ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ የተዘረዘሩትን ግሶች በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- መምህሩ ተማሪዎችን አስተማረ፡፡

አስተማረ ጻፈ አመነ መጠጠ መሰከረ ነገደ ቀጠፈ ሞረደ

ሐ. ቀጥሎ በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ሦስት የተለያዩ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሠረት መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- በዓላትን ተሰባስቦ ማክበር ደስ ይላል፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በዓላትን | ይዞ | ለወላጆቻችን | ወንድሙን | ጨዋታ |
| ስንጨርስ | ተሰባስቦ | ሰኞ ማክሰኞ | ማክበር | ምርቃት |
| አጠናን፡፡ | ተቀበልን፡፡ | ተመለሰ፡፡ | ተጫውተን | በመታዝ |
| | | ደስ ይላል፡፡ | | |

## መ. በምሳሌው መሠረት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- የልጆች ጨዋታ -"መጩ ተኬ"


መጩ ተኬ አንዱ የልጆች ጨዋታ ነው፡፡ ለጨዋታው ቢያንስ ሁለት ልጆች ያስፈልጋሉ፡፡ ለመጫወቻ የሚሆን ከእጃችን መዳፍ የሚያንስ ሁለት ጠፍጣፋ ድንጋይ እናዘጋጃለን፡፡ የድንጋዩ ስም "ከምች" ይባላል፡፡ ጨዋታውን አንዱ ልጅ ቀድሞ ይጀምራል፡፡ ጨዋታውን የሚጀምረው ልጅ አንዱን ድንጋይ (ከምች) መሬት ላይ በተወሰነ ርቀት ይጥለዋል፡፡ ድንጋዩን በሌላ ድንጋይ (ከምች) ይመታዋል ወይም ያጋጨዋል፡፡ ድንጋዩን ከመታው ጓደኛው ያዝለወል፡፡ የተመታው ድንጋይ ድረስም ይወስደዋል፡፡ከሳተው ደግሞ ጓደኛውን ያዝለዋል፡፡ የሳተው ድንጋይ ድረስ ይወስደዋል፡፡ በዚህ ህግ ተራ በተራ ጨዋታው ይቀጥላል፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡

## ስግብግቡ አይጥ



አንድ ስግብግብ አይጥ በበቆሎ የተሞላ ቅርጫት አየና ሊበላ ፈለገ፡፡ ስለዚህ ቅርጫቱን በጥርሱ ቦርቡሮ ትንሽ ቀዳዳ ሠራ፡፡ በዚያች ቀዳዳም ወደ ቅርጫቱ ውስጥ ገባ፡፡ በዚያ ውስጥም ሆኖ ብዙ በቆሎ በላ ከዚያ በጣም ተደሰተ፡፡ እንደልቡ መጥገቡን ሲያረጋግጥ ለመውጣት ፈለገ፡፡ አስቀድሞ በሠራት በትንሿ ቀዳዳ በኩል ለመውጣት ሞከረ፡፡ ግን አልቻለም፡፡ ሆዱ ሞልቷል፡፡ እንደገና ሞከረ፡፡ ግን በቀዳዳው አልፎ መውጣት አልቻለም፡፡ አይጡ ማልቀስ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ጥንቸል በቅርጫት አጠገብ እያለፈ ነበር፡፡ የአይጡን ጩኸት ሰምቶ “ወዳጄ ለምን ታለቅሳለህ?” አለው፡፡ ያኔ አይጡ “በቆሎውን ለመብላት ብዬ ትንሽ ቀዳዳ ሰርቼ ወደ ቅርጫቱ ውስጥ ገባሁ፤ አሁን በዚያ ቀዳዳ በኩል መውጣት አልቻልኩም፡፡ ” አለ፡፡ ጥንቸሉም “ብዙ ስለበላህ ነው፤ ሆድህ እስኪቀንስ ጠብቅ፡፡” ብሎት እየሳቀ ሄደ፡፡







አማራጭ ያጣው አይጥ በቅርጫት ውስጥ እንዳለ እንቅልፍ ያዘው፡፡ በማግስቱ ጠዋት ሆዱ ቀንሷል፡፡ እሱ ግን ከቅርጫቱ ውስጥ መውጣት እንዳለበት ረስቶ ጥቂት ተጨማሪ በቆሎ መብላት ፈለገ፡፡ ስለዚህ በቆሎውን በልቶ ሆዱ በድጋሚ ተቆዘረ፡፡ ጠግቦ ከበላ እና ቁንጣን ከያዘው በኋላ ከቅርጫቱ ወጥቶ ማምለጥ እንዳለበት አስታወሰ፡፡ ግን የማይሆን ነገር ነው፤ አልቻለም፤ እናም በድጋሚ “ኦ! አሁንም ነገ እወጣለሁ፡፡” ብሎ አሰበና ተኛ፡፡ ግን በቀጣዩ ቀን በዚያ የበቆሎ ቅርጫት በኩል ታልፍ የነበረው ድመቷ ነበረች፡፡ ምን ያጋጥመው ይሆን?

(ምንጭ፡- NeBeb ንበብ፡ Reading Platform ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተጣጥሞ የቀረበ)

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## መናገር

**የሚከተሉትን የሰውነት ክፍሎች በግእዝ ስያሜያቸው ምን እንደሚባሉ ካጠናችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ በቃል አቅርቡ፡**

| የሰውነት ክፍሎች ስዕል | አማርኛ | ግእዝ | የሰውነት ክፍሎች ስዕል | አማርኛ | ግእዝ |
|---|---|---|---|---|---|
|  | ራስ | ርእስ |  | አፍ | አፍ |
|  | ፀጉር | ስእርት |  | ከንፈር | ከንፈር |
|  | ፊት | ገጽ/ ልታሕት |  | ጥርስ | ሥን |
|  | ግንባር | ፍጽም |  | አገጭ | ሕልቅ |
|  | ዓይን | ዓይን |  | ጣት | አፃብዕ |
|  | ቅንድብ | ቀርነብ |  | ጉልበት | ብረክ |
|  | ጆሮ | እዝን |  | እጅ | እድ |
|  | አፍንጫ | አንፍ |  | እግር | እግር |

# የምዕራፍ ዘጠኝ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሃጫ | ደንብ | ገለጸ |
| ለሆሳስ | ስውር | ወጠነ |

2. ጥገኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም አምስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

3. የሚከተሉትን አገላለጾች አሟሉ፡፡

ምሳሌ፦ ሎሚ የመሰለ ተረከዝ ካልን፦

ሀ. ድሪ የመሰለ______________እንላለን፡፡

ለ. ሳንቃ የመሰለ______________እንላለን፡፡

ሐ. ብርሌ የመሰለ______________እንላለን፡፡

መ. አለንጋ የመሰለ______________እንላለን፡፡

4. ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን ወይም ከሌሎች የመገናኛ ብዙኃን የሰማችሁትን አስተማሪ መረጃ ከ5 እስከ 7 በሚሆኑ ነጠላ ዓረፍተነገሮች በመጠቀም በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

# ምዕራፍ 10

# ንግድ

## የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ:-

- አዳምጣችሁ በቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ።
- ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ዋናውን ሃሳብ ትለያላችሁ።
- በተሰጣችሁ ርእስ አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- ከአንድ በላይ ፍች ያላቸውን ቃላት ትፈልጋላችሁ።
- ቅጥያዎችን ተጠቅማችሁ ዐረፍተነገር ትመሰርታላችሁ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማዳመጥ

#### ንግድ





### ቅድመ ማዳመጥ

ሀ. ንግድ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. በምትኖሩበት አካባቢ የንግድ ተቋማት አሉ? ካሉ ምን ምን አይነት የንግድ ተቋማት እንደሆኑ ተናገሩ?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መናገር

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በቃል አብራሩ፡፡

1. አንድ ነጋዴ ትርፋማ ለመሆን ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
2. ነጋዴ ኪሳራ የማይገጥመው ምን ሲሆን ነው?
3. ደንበኛን በጥሩ ስነ-ምግባር ማስተናገድ ለምን የሚጠቅም ይመስላችኋል?
4. ገንዘብ ብቻ መኖሩ ለስኬት አያበቃም ሲል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ፡፡
5. የንግድ ሥራ ለአንድ አገር የሚሰጠውን ጥቅም ተናገሩ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተግባር አንድ፡- ቃላት

ሀ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መመዘኛ | ሀ. ችሎታ |
| 2.አጋዥ | ለ. ማፍለቅ |
| 3.መፈለግ | ሐ. መለኪያ |

4.ማመንጨት መ. መሻት

5.ክህሎት ሠ. ደጋፊ

ለ. በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አተረፈ | ሀ. ተጎጂ |
| 2. ተጠቃሚ | ለ. ማዋረድ |
| 3. ውጫዊ | ሐ. መጓደል |
| 4. ማክበር | መ. ከሰረ |
| 5. መሟላት | ሠ. መውጣት |
| | ረ. ውስጣዊ |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

[illegible]

ሀ. ከዚህ በታች በቀረበው የአንቀጽ ምሳሌ መሠረት የተከታዩን አንቀጽ ዋና መልዕክት (ሐሳብ) ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

እኛ ኢትዮጵያውያን በአብሮነት አኗኗራችን ከመሠረትናቸው ጠንካራ እሴቶቻችን መካከል አንዱ በሀዘን ጊዜ መደጋገፍ እና እርስ በእርስ መጽናናት ነው፡፡ ለዚህም ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ደግሞ ማህበራዊ መሰባሰቢያችን የሆነው እድር ነው፡፡ እድር መግባት የሚያስከትለው ሃለፊነት እና ግዴታ እንዳለ ሆኖ ሰው ሆኖ የማይደሰት እንደሌለ ሁሉ ሃዘን የማይገጥመው የለም፡፡


ታዲያ በዚህ ጊዜ ያዘነ ሰው ከሃዘኑ እንዲላቀቅ ለማጽናናት ብሎም ከሃዘን ጋር ተያይዞ ለሚገጥመው ወጪ ድጋፍ እና አለው ባይነትን ከማህበረሰቡ

የሚያገኝበት እርስ በእርስ የምንተጋገዝበት ትልቅ ኢትዮጵያዊ የማህበራዊ አብሮነት ማሳያ መሰባሰቢያችን የሆነው እድር ነው፡፡

የአንቀጹ ዋና መልዕክት፡- የኢትዮጵያዊ አብሮነት ማሳያዎች ከሆኑት አንዱ እድር መሆኑን እና ያለውን ጠቀሜታ የሚያሳይ ማሳየት ነው፡፡

1. ከዚህ በታች የተጻፉት አንቀጾች ዋና ሃሳባቸው ምንድን ነው?


ገበጣ የኢትዮጵያ ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ይህን ጨዋታ ሁለት ሰዎች የሚጫወቱት ነው፡፡ በገበጣ ጨዋታ ህግ መሠረት ገበቴው ላይ 18 ጉድጎዶች ሲኖሩ የተወሰኑ ጠጠሮችም በየጉድጓዱ ይቀመጣሉ፡፡ የጨዋታው አላማ እንግዲህ የባላጋራን ጠጠሮች መብላት ነው፡፡ የባላጋራ ጠጠሮች ዜሮ ሲቀሩ ያንጊዜ ተጫዋቹ አሸነፈ ይባላል፡፡



2. መደበኛ ትምህርትን ትምህርት ቤት ገብተን በመማር ሰዓት ኖሮት በሙያው ላይ የሰለጠኑ መምህራን ተመድበውለት የሚሰጥ ትምህርት መደበኛ ትምህርት ይባላል፡፡ በአገረችን መደበኛ ትምህርት ከአጸደ ሕጻናት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የሚሰጥ ሲሆን ዋና አላማው ሰዎች የሚጠቀሙበትን እውቀት ማስጨበጥ ነው፡፡


ለ. በምሳሌው መሠረት ከታች የተሰጠውን ምስል በመመልከት በእያንዳንድዱ ምስል አንዳንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-



ይህ ምስል የሚያሳየን የእንስሳቱን እና የዕጽዋቱን የምግብ ሰንሰለት ትስስር ነው። በትስስሩ መሠረት ሕይወት ካላቸው አራቱ ነገሮች መካከል በቅድሚያ እጽዋቱ ለመኖር የተለያዩ መዓድናትን እና ውሃን በስሩ አማካኝነት ከመሬት በማግኘት እና በፀሀይ ብርሃን ምግቡን በማዘጋጀት ያድጋል። አይጥ ደግሞ በሕይወት ለመቆየት እጽዋቱን ይበላል። ምክንያቱም አይጥ ሥጋ እና ዕፀዋትም ተመጋቢ በመሆኑ። በመቀጠል ሥጋ በል በሆነው እባብ አይጡ ይበላል። በተመሳሳይ እባቡ ደግሞ በጭልፊት (አሞራ) ይበላል ማለት ነው።

1.



2.



# ክፍለ ትምህርት አራት

## ንባብ

## መልካም ሰው



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. አንድ ሰው መልካም ሰው የሚባለው ምን አይነት ተግባራትን ሲፈጽም ነው?

ለ. እናንተ የፈጸማችሁት መልካም ተግባር ካለ ተናገሩ?

ሱራፌል ይባላል፡፡ ሱራፌል በወልቂጤ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ካሉ የትላልቅ ሆቴሎች ባለሀብቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሱራፌል ከሆቴል ንግድ ሥራው ጎን ለጎን በበጎ አድራጎት እና በከተማ ልማታዊ ሥራዎች ላይም ይሳተፋል፡፡ ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከልጅነቱ ጀምሮ በየመንገዱና በየመኪናው መስኮት እየዞረ ማስቲካ፣ ሶፍት እና ብስኩት በመሸጥ የሚያገኘውን ትርፍ በማጠራቀም ዘወትር ቅዳሜ ቅዳሜ ባንክ እየሄደ ያስቀምጥ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ለተከታታይ አምስት አመታት ያስቀመጠው ገንዘብ ስልሳ ሺህ ብር ደረሰለት፡፡

ከዚህ በኋላ “በዚህ ገንዘብ ተጨማሪ ሥራ ብሠራበት ይሻላል፡፡” በሚል ባንክ ካጠራቀመው ስልሳ ሺህ ብር ላይ ሃምሳ ሺህ ብር በማውጣት በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ በተሰጠው ትንሽ ብረት በብረት የሆነች ቤት ውስጥ ቁርስ ቤት ከፈተ፡፡ በከፈተው ቁርስ ቤት እንደ ቡና፣ ሻይ፣ ወተት የመሳሰሉትን

ትኩስ ነገሮችንና እንዲሁም ሽሮ፣ ፍርፍር፣ ብስኩት እና ዳቦ የምግብ ዓይነቶችን እያዘጋጀ መሥራት እና መሸጥ ጀመረ። የሚያዘጋጀውም ምግብ ጥራት ስለነበረው ከሩቅም ከቅርብም ደንበኛ በርከትከት ማለት ጀመረ። በሃምሳ ሺህ ብር የጀመረው ቁርስ ቤት ገቢውን ከማሳደግ አልፋ ከብዙ ሰዎች ጋር እንዲተዋወቅ አደረገችው።

ባለታሪኩ ካለው የስራ ፍላጎት በመነሳት ንግዱ የት ደረጃ የሚደርስ ይመስላችኋል?

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ተጨማሪ ገንዘብ ከባንክ ብድር ወስዶ ከቁርስ ቤቷ በተጨማሪ ሰፋ ያለ ቤት ተከራይቶ የሆቴል ንግድ ሥራን ተያያዘው። ለወትሮውም ስመ-ጥርና ታታሪ የነበረው ሱራፌል ዝናውን የሰሙ ሰዎች ወደ ሆቴሉ መጉረፍ ጀመሩ። በሆቴል ሥራውም ከራሱ አልፎ በውስጡ ከሃያ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር ቻለ። ከመንግስት የሚጠየቀውን ግብርም በሰዓቱ ስለሚከፍል በየአመቱ በርካታ የምስክር ወረቀት ይሸለማል። ትናንት በየመንገዱ ማስቲካና ሶፍት እያዞረ ሲሸጥ የነበረው ሱራፌል የሚያገኘውን ገቢ በአግባቡ በመቆጠቡ ዛሬ የትልቅ ሆቴል ባለቤት ለመሆን በቅቷል።

ሱራፌል ከንግድ ሥራዉ ጎን ለጎን በክፍለ ከተማው የሚገኙ ባለሀብቶችንና የመንግስት ባለስልጣናትን በማወያየት የህፃናት መርጃ ድርጅት የሚል የበጎ አድራጎት ማሕበር አቋቁሟል። ከ150 በላይ የሚሆኑ ሕፃናትንም በሕፃናት መርጃ ድርጅቱ ውስጥ በማቀፍ ከዕለት ጉርሳቸው እስከ ዓመት ልብሳቸው አልፎ ተርፎም የትምህርት ቁሳቁሳቸውን ሁሉ ያሟላላቸዋል።

የተለያዩ የልማት ሥራዎች በሚሰሩበት ጊዜም የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር በኩል የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። በመሆኑም በዚህ ዓመት ለደረሰበት መልካም ውጤት ሽልማትን ተቀበለ።

# አንብቦ መረዳት ጥያቄ

## ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

1. ሽልማት የተሰጠው ምን አይነት ሥራ ስለሠራ ነው?

2. ባለታሪኩ በልጅነቱ ምን አይነት ሥራ ይሠራ ነበር?
3. ገንዘብ መቆጠብ ለምን ይጠቅማል?
4. ሱራፌል ሕዝቡን በማስተባበር በኩል ያንበሳውን ድርሻ ይወስዳል ሲል ምን ለማለት ነው?

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## መናገር

የምንባቡን ዋና መልዕክት ወይም ሐሳብ በአምስት ዓረፍተ ነገሮች አጠቃላችሁ ጻፉ፡፡ በመቀጠል ስለዋናው መልዕክት የቡድን ውይይት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ አቅርቡ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ቃላት

ሀ. በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መጉረፍ | ሀ. መልካም |
| 2. ማቀፍ | ለ. ማጠራቀም |
| 3. በጎ | ሐ. በብዛት መምጣት |
| 4. በረከተ | መ. መያዝ |
| 5. መቆጠብ | ሠ. በዛ |

ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

1. ልማት
2. አወጣ
3. ዓመት
4. አተረፈ
5. መቅረት

# ክፍል ትምህርት ሰባት

## ????

**ሀ. የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚያሳዩትን ትርጉም በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡-

- ከመጫወት ይልቅ ሥራችን በአግባቡ <u>እንሥራ</u>፡፡
  (ሲጠብው = እናከናውን/ እንተግብር)
- <u>እንሥራ</u> ከሸክላ አፈር የሚሠራ ቁስ ነው፡፡
  (ሲላላ = ለውሃ መያዣነት የሚያገለግል ባህላዊ ቁስ)

| | |
|---|---|
| 1. ገዳም | 3. ግጥም |
| 2. ጥሬ | 4. ወጥ |

**ለ. ከሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቅጥያዎችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ውጤታማ = ውጤት - ኣማ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውጤታማ | ልብሳቸው | ግብዓት | መኪናዬ |
| ሴትነት | ቤታችን | ፈረሶች | ዶሮዎቹ |

ሐ. በሳጥኑ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ እና መስተፃምር መሆናቸውን ለይታችሁ በየምድባቸው አስቀምጡ።

አተረፈ | ነገደ | ረጅም | ተራራ | ወይም

ገዢያ | ጠይም | እና | አስተማሪ | ገመጠ

ገላጭ
1.
2.
3.
4.

ስም
1.
2.
3.
4.

ግስ
1.
2.
3.
4.

መስተጻር
1.
2.
3.
4.

መ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ።

መስተጻር | መንደራችን | መምህሮች | ነጻነት

መንገደኛ | መንፈሳዊ | ትርፋማ

ምሳሌ:- በመደርደሪያው ላይ በርካታ ሹካዎች ተቀምጠዋል።

ሠ. በምሳሌው መሠረት ሚከተሉት ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ደረሰ

- ወደቤቱ በጊዜ ደረሰ፡፡ (ትርጉሙ= በሰዓቱ ተመለሰ)
- መጽሀፍ ደረሰ፡፡ (ትርጉሙ = ጻፈ)

1. ጠላ
2. አሰሰ
3. ሳሳ
4. ሥጋ
5. ቀጠፈ

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ነጠላ ዓረፍተነገሮች

ረ. ከታች የቀረበውን አንቀፅ በማንበብ አራት ነጠላ ዓረፍተነገሮችን አውጡ፡፡

አርባ ምንጭ በደቡብ ክልል ከሚገኙ የፍራፍሬ ቦታዎች አንዱ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ በስፋት ሙዝ ይመረታል፡፡ ነጋዴውም ከተለያዩ ቦታዎች በመምጣት በስፋት ሙዝ ይገዛል፤ በመኪና በመጫንም በአገሪቱ ላሉ የተለያዩ አካባቢዎች ያዳርሳሉ፡፡ በአሁን ሰአት በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በስፋት ገበያ ላይ የምናገኘው ይህንኑ የአርባ ምንጭ ሙዝ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ዞን የአፕል ምርት በስፋት ይመረታል፡፡ አረሶ አደሩም ፍራፍሬዎችን በማምረት በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ እየሆነ ይገኛል፡፡ ይህም የሚየሳየው አርሶ አደሩ ጠንክሮ ከሠራ በብዙ መንገድ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ነው፡፡

ምሳሌ፡- በአርባምንጭ በስፋት ሙዝ ይመረታል፡፡

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## አቀላጥፎ ማንበብ

*መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀ አንቀጽ አንብቡ፡፡*

### አህያና ውሻ

በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ አንድ ውሻና አንድ አህያ ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አህያዋ ለውሻው እንዲህ አለችው፡፡ ‹‹እኔ ሥራ ስለበዛብኝና እዚህ ቤት መኖር ስለሰለቸኝ ልጠፋ ነው፡፡›› ብላ አማከረችው፡፡ ውሻውም ካዳመጣት በኋላ ‹‹እኔም እዚህ ቤት መኖር ሰልችቶኛልና አብሬሽ መጥፋት እፈልጋለሁ፡፡›› አላት፡፡ በዚህም ተስማምተው ሁለቱም ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ ብዙ ርቀት ከተጓዙ በኋላ ፀሀይ እየጠለቀች ምሽቱ እየገፋ ሲመጣ አንድ ሣር ያለበት ሜዳ ላይ ደረሱ፡፡ አህያዋም እርቧት ስለነበረ ሣር መጋጥ ጀመረች፡፡ ውሻውግን የሚበላ ነገር ስላላገኘ ሜዳው ላይ ተቀመጠ፡፡
አህያዋ ብዙ ሣር ግጣ ከጠገበች በኋላ ለውሻው ‹‹አንዴ ላናፋ ነው፡፡›› አለችው፡፡ ውሻውም ‹‹ምን ነካሽ ካናፋሽ በጅብ መበላትሽ ነውና ይቅርብሽ፡፡›› ቢላትም ሜዳውን እየዞረች ካናፋች በኋላ በድጋሚ ሣር መጋጥ ቀጠለች፡፡ ለሁለተኛ ጊዜም ስትጠግብ ለውሻው ‹‹ላናፋ ነው፡፡›› ብላው ሜዳውን እየዞረች አናፍታ ስትጨርስ ሣር መጋጧን ቀጠለች፡፡ አሁንም ጥቂት ጊዜ ከቆየች በኋላ ውሻውን ‹‹እባክህን ፍቀድልኝና ለመጨረሻ ጊዜ ላናፋ፡፡›› አለችው፡፡ ውሻው ግን ‹‹ተይ የመጀመሪያው ማናፋት ለጅቡ መጥሪያ፤ ሁለተኛው ደግሞ ጅቡን ማቅረቢያ፤ በሶስተኛው ግን መበላትሽ ነውና ይቅርብሽ፡፡›› አላት፡፡ አህያዋ ግን ምንም አይመጣም ብላ ሜዳውን እየዞረች ድምጿን ከፍ አድርጋ ስታናፋ ጅቡ ዘሎ ሆዷን ዘርግፎ ገደላት፡፡ ውሻውም በአህያዋ መበላት በጣም ደንግጦና ባደረጋት ነገር ተጸጽቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

# የምዕራፍ አስር የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሰይ እና ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡ በመቀጠልም ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ዘመድ | አጣላ | አንጋጠጠ |
| አቀረበ | ሰባ | መራራ |

2. የሚከተሉትን ቃለት በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሲገቡ የሚኖራቸውን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መሥርቱ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ቆረጠ | ሐ. ገዛ | ሠ. አረረ |
| ለ. ሰፋ | መ ምሳ | |

3. የንባብ ጥቅምን የተመለከተ ከ5-7 ኣረፍተ ነገሮችን የያዘ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

# ቃላት ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| ህቡዕ | ድብቅ፣ ምስጢራ፣ ይፋ ያልሆነ |
| ለቀቀ | በስድ አሳደገ፣ አባለገ፣ ፈታ፣ ነፃ አደረገ፣ ተወ |
| ለተመ | በኃይል አጋጨ፣ መታ |
| ለገሰ | ቸረ፣ ናኘ፣ ሰጠ |
| ሊቅ | በትምህርት የበሰል፣ የተራቀቀ ሙሁር፣ አዋቂ |
| ሳቀ | በለጠ፣ አደገ፣ በረታ፣ ከፍ አለ |
| መለሎ | ቀጥ ያለ፣ ረዥም፤ ሽንቅጥ ያለ፣ መዘዞ |
| መረን | ስድ፣ ልቅ፣ አግድም አደግ፣ ባለጌ፣ ያልተቀጣ |
| መሰሪ | ሸረኛ፣ ተንኮለኛ፣ ለበጎም ለክፉም ነገር የሚጠበብ |
| መርሃ-ግብር | የሥራ መመሪያ፣ ዕቅድ፣ ፕሮግራም |
| መሻት | መፈለግ፣ መፍቀድ፣ መመኘት |
| መነመነ | ከሳ፣ ቀጠነ፣ ሞገገ፣ ኮሰመነ፣ ሟሸሸ |
| መነዘረ | ሸረፈ፣ ተነተነ፣ ለወጠ፣ በተነ |
| መዘንጋት | መርሳት |
| ረግረግ | ውሃማ ቦታ |
| ተራራ | አዘነ፣ ማረ፣ ይቅር አለ |
| ራሰ | ረጠበ፣ ተነከረ |

| | |
|---|---|
| ሰለቸ | ታከተ፣ ተንገፈገፈ፣ ተማረረ፣ ተንገሸገሸ |
| ሰመረ | አማረ፣ ተዋጣ፣ ተሳካ፣ ወደደ |
| ሰረገ | ደገሰ፣ ዳረ፣ ሰመጠ፣ ወደ ውስጥ ገባ፣ ወደመሬት ውስጥ ገባ |
| ሲሳይ | እህል፣ ምግብ፣ ሃብት፣ አዱኛ፣ በረከት |
| ሳንቃ | ለበር መዝጊያ የሚሆን ጠፍጣፋ እንጨት |
| ሸመተ | ገዛ፣ ገበየ፣ ለወጠ፣ አተረፈ |
| ቀላቀለ | አደባለቀ፣ አገናኘ፣ ቀየጠ |
| ቀማኛ | ወንበዴ፣ ዘራፊ፣ የሚነጥቅ |
| ቅርስ | የሰው፣ የእንስሳት፣ የዕፅዋት ቅሪት፣ የተጠራቀመ ሃብት |
| በለጸገ | ከበረ፣ ሐብታም ሆነ |
| ተመረቀ | ተባረከ፣ በረከት አገኘ |
| ተጋ | ፈጠነ፣ ነቃ፣ በረታ፣ ጎበዘ፣ |
| ታተረ፣ | ከስንፍና ራቀ |
| ታነፀ | ተገነባ፣ ተቀረፀ |
| ትሁት | ቅን፣ ገር፣ ታዛዥ፣ ስነ-ስርዓት አክባሪ |
| ነሰነሰ | ጎዘጎዘ፣ በተነ፣ ረጨ፣ ዘረዘረ |
| ይፋ | ግልፅ |
| ንዋይ | ሀብት፣ ንብረት |
| አለቃ | መሪ፣ ሹም፣ ዋና፣ ሊቅ፣ አዋቂ |
| አላመጠ | አኘከ፣ አደቀቀ፣ በላ፣ ስም አጠፋ፣ |
| አማ | |

| | |
|---|---|
| አላቀቀ | ለያየ፣ በታተነ፣ ገነጣጠለ |
| አርዓያ | ምሳሌ፣ አብነት፣ አምሳል፣ የመልካም ምሳሌ |
| አበረከተ | ሰጠ፣ አበዛ |
| አያሌ | በጣም ብዙ፣ በርካታ |
| አናፋ | ጮኸ(ለአህያ)፣ ጉራውን ነዛ |
| አንቱታ | ከበሬታ |
| ወላወለ | አመነታ፣ ተጠራጠረ፣ አፀዳዳ፣ ጠራረገ |
| ውብ | ቆንጆ፣ ያማረ፣ ለዛ ያለው |
| ዛለ | ደከመ፣ ተልፈሰፈሰ፣ አቅም አጣ |
| ደባ | ተንኮል፣ ሴራ፣ ክፋት |
| ደንበኛ | ታማኝ፣ ዘወትር ካንድ መደብር እቃ የሚገዛ |
| ደጎመ | ረዳ፣ ደገፈ፣ በጎደለ ሞላ |
| ድል | ማሸነፍ፣ አሸናፊነት |
| ጀብድ | ጀግንነት፣ ደፋር |
| ጃጀ | አረጀ፣ አፈጀ፣ ሸመገለ |
| ገበያ | መግዣ፣ መሸጫ፣ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ቦታ |
| ገባር | መጋቢ |
| ጦስ | ምክንያት፣ መዘዝ፣ ሰበብ፣ችግር |
| ጫና | ከባድ ሸክም፣ ጭቆና |
| ጮሌ | ብልጥ፣ ፈጣን |
| ፀዳ | ንፁህ ሆነ፣ ነፃ |
| ፀፀት | ሐዘን፣ ንስሐ፣ ትካዜ፣ የቁጭት ስሜት |
| ፅናት | ጥንካሬ፣ ብራታት |
| ፈተነ | ሞከረ፣ ፈተሸ |

ፈፀመ ጨረሰ፣ ቋጨ፣ አጠናቀቀ፣ አደረገ፣ ሠራ

ፌሽታ የደስታ መግለጫ

ፍርድ ብይን፣ ዳኝነት፣ ውሳኔ፣ ፍትህ

ፍቅር መውደድ፣ ግብቡ፣ ስምሙ፣ እጅግ በጣም ጥልቅ የሆነ መዋደድ

# ዋቢ ጽሑፎች

ለማ ጉያ (1995 ዓ.ም)፡፡ ያላስተማሪ የሥዕል ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ፡፡ አ.አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃለት ሐዲስ፤ (1948ዓ.ም)፡፡ በአርቲስቲክ ማተሚያቤት ታተመ፡፡

ሺበሺ ለማ(2007ዓ.ም)፡፡ አርዓያዎቹ፡፡ ሜጋ ኣሳታሚ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር፡፡

በትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማኑዋል፡፡(2011 ዓ.ም)፡፡ ንቁ በርታ ማተሚያ ቤት፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር፡፡ (2009 ዓ.ም)፡፡ አጋዥ መጽሀፍ ለንባብ ትምህርት፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት፡፡ (2013ዓ.ም)፡፡ ዝክረ ህዳሴ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህረትቢሮ(2004ዓ.ም)፡፡ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ፡፡አል-ጉርኤር አሳታሚ እና አከፋፋይ፡፡

በፎረም ሶሻል ስተዲስ እና በብሪቲሽ ኤምባሲ(በ2007ዓ.ም)፡፡ የሕዝብ አገልግሎቶች አሰጣጥ በአዲስ አበባ

ባህሩ ዘርጋው (1994 ዓ.ም)፡፡ ዘርጋው መለስተኛ የአማርኛ መዝገበቃላት፡፡ ርኖቦት ሚዲዎች፡፡

ባዬ ይማም (2004 ዓ.ም)፡፡ አጭርና ቀላል የአማረኛ ሰዋስው፡፡ አልፋ ፕሪንተር፡፡

ብርሃኑ ሀብተማሪያም(1997ዓ.ም)፡፡ ውሃ ሕይወት ነው፡፡ በት.መ.ማ.ማ.ድ ታተመ

ተክለማርያም ፋንታዬ(1964ዓ.ም)፡፡ ኖኀተ ጥበብ ዘሥነ-ጽሑፍ፡፡ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ቱሪዝም አዲስ 6ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8፣ (2001ዓ.ም)፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አዲሰ ዘመን ጋዜጣ (2011 ዓ.ም)፡፡ 78ኛ ዓመት፤ መጋቢት 1፡፡ ቁጥር

181፡፡
አዲስ ዘመን (2011ዓ.ም)፡፡ 78ኛ ዓመት ፤ መጋቢት 23ቁጥር 203፡፡
አዲስ ዘመን ጋጤጣ (2012 ዓ.ም)፡፡ 79ኛ ዓመት ሚያዚያ 7፤ ቁጥር 217፡
፡
የኢትዮጵያ ሬድዮ ለ80ኛ ዓመት የተዘጋጀ ልዩ መጽሔት (2013ዓ.ም)፡፡
እሸቱ አሰፋ፡፡(2000ዓ.ም)፡፡ ፕላኔቶችና ሌሎች የሰማይት አካለት፡፡
ከህጻናት መዝሙር ላይ ተወሰደ ያልታተመ
ዳንዔል ወርቁ(2011ዓ.ም)፡፡ የጣና አቤቱታ፡፡ ወርልድ ቪዥን፡፡
--------------(2011ዓ.ም)፡፡ ወርቃማው ዓሣ፡፡ ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ፡፡
ፈቃደ አዘዘ (1991ዓ.ም)፡፡ የስነ-ቃል መምሪያ

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ሀምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| ከ1 እስከ 10 | | ከ11 እስከ 20 | |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች | የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፩ | 1 | ፲፩ | 11 |
| ፪ | 2 | ፲፪ | 12 |
| ፫ | 3 | ፲፫ | 13 |
| ፬ | 4 | ፲፬ | 14 |
| ፭ | 5 | ፲፭ | 15 |
| ፮ | 6 | ፲፮ | 16 |
| ፯ | 7 | ፲፯ | 17 |
| ፰ | 8 | ፲፰ | 18 |
| ፱ | 9 | ፲፱ | 19 |
| ፲ | 10 | ፳ | 20 |

| ከ20 እስከ 100 | | ከ200 እስከ 1000 | |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች | የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳ | 20 | ፪፻ | 200 |
| ፴ | 30 | ፫፻ | 300 |
| ፵ | 40 | ፬፻ | 400 |
| ፶ | 50 | ፭፻ | 500 |
| ፷ | 60 | ፮፻ | 600 |
| ፸ | 70 | ፯፻ | 700 |
| ፹ | 80 | ፰፻ | 800 |
| ፺ | 90 | ፱፻ | 900 |
| ፻ | 100 | ፲፻ | 1000 |

| ከ2000 እስከ 10000 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 |
| ፵፻ | 4000 |
| ፶፻ | 5000 |
| ፷፻ | 6000 |
| ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 |
| ፺፻ | 9000 |
| ፼ | 10000 |